# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ
## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

ሰዋስው
ቃላት
መፃፍ
ሥነ-ጽሑፍ
መናገር
ማንበብ
ማዳመጥ

## 8ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# ለመፅሐፉ ሊደረግ ስለሚገባው የአያያዝ ጥንቃቄ

የመማሪያ መፅሀፋችሁ የትምህርት ቤቱ ንብረት ቢሆንም እንደራሳችሁ ንብረት መያዝ ይኖርባችኋል፡፡ እንዳይጠፋም ጥንቃቄ አድርጉ፡፡

1. መፅሀፉን በቀላሉ እንዳይበላሽ በጠንካራ ወረቀት ሽፍኑት

2. መፅሐፉን ደረቅና ቆሻሻ በሌለበት ቦታ አስቀምጡት፡፡

3. መፅሀፉን ለመጠቀም ስትፈልጉ እጃችሁን አፅዱ፡፡

4. በመፅሀፉ ሽፋንም ሆነ የውስጥ ገፆች ላይ በፍፁም አትፃፉ፤ ስዕሎችንም

   አትሳሉ፡፡

5. ለመፅሀፉ ገፅ መለያ ወይም እልባት ስትፈልጉ ጠንካራ ወረቀት ወይም

   ክር ተጠቀሙ እንጂ ገፁን አትጠፉ፡፡

6. በመፅሀፍ ውስጥ ያሉትን ገልፆች ወይም ስዕሎች ገንጥላችሁ

   አታውጡ፡፡

7. የመፅሀፉ ሽፋን ወይም ገፅ ከተገነጠለ በማስትሽ አያይዙ፡፡

8. መፅኀፉ ቦርሳ ውስጥ ሲገባና ሲወጣ እንዳይጨማደድ ጥንቃቄ

   ማድረግ፡፡

9. መፅሀፉን ለሌላ ሰው ስታውሱም ሆነ ስትዋሱ እንዳይቀደድ ጥንቃቄ

   አድርጉ፡፡

# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 8ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# አማርኛ

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 8ኛ ክፍል


አዘጋጆች

ማርሸት ክበበው(ኤም.ኤ)

የሰውዘር በለጠ(ኤም.ኤ)

የትምወርቅ ዘውዴ(ኤም.ኤ)

ገምጋሚዎች፡-

ለዝና መንግስቴ (ቢ.ኢ.ዲ)

ነፃነት ጥጋቡ(ኤም.ኤ)

ይሻሙ ጌራወርቅ(ኤም.ኤ)

# ማውጫ

ምዕራፍ ገጽ

1 ምዕራፍ አንድ፡-ሀገር በቀል እውቀቶችና ባህሎች--------------1

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ----------------------------------------2

ክፍል ሁለት፡- መናገር-------------------------------------------3

ክፍል ሶስት፡- ማንበብ-------------------------------------------3

ክፍል አራት፡- መጻፍ---------------------------------------------6

ክፍል አምስት፡- ቃላት-----------------------------------------7

ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው---------------------------------------8

ክፍል ሰባት፡- ሥነ-ጽሁፍ ------------------------------------11

2 ምዕራፍሁለት፡- ሳይንስና ቴክኖሎጂ---------------------------14

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ---------------------------------------14

ክፍል ሁለት፡- መናገር------------------------------------------15

ክፍል ሶስት፡- ማንበብ------------------------------------------16

ክፍል አራት፡- መጻፍ--------------------------------------------21

ክፍል አምስት፡- ቃላት----------------------------------------24

3 ምዕራፍ ሶስት፡- ተላላፊ በሽታዎች-----------------------------27

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ---------------------------------------28

ክፍል ሁለት፡- መናገር------------------------------------------29

ክፍል ሶስት፡- ማንበብ------------------------------------------30

ክፍል አራት፡- መጻፍ--------------------------------------------33

ክፍል አምስት፡- ቃላት----------------------------------------34

ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው--------------------------------------35

ክፍል ሰባት፡- ሥነ-ጽሁፍ ------------------------------------37

4. ምዕራፍ አራት፡- ግጥም-----------------------------------------40
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ --------------------------------------41
ክፍል ሁለት፡- መናገር---------------------------------------42
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ-----------------------------------------42
ክፍል አራት፡- መጻፍ------------------------------------------46
ክፍል አምስት፡- ቃላት----------------------------------------48
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው--------------------------------------49
5 ምዕራፍ አምስት፡- አርበኝነት------------------------------ --57
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ------------------------------------ --58
ክፍል ሁለት፡- መናገር-----------------------------------------49
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ-------------------------------------------60
ክፍል አራት፡- መጻፍ--------------------------------------------66
ክፍል አምስት፡- ቃላት------------------------------------------66
ክፍል ስድስት፡-ሥነ-ጽሁፍ--------------------------------------67

6 ምዕራፍ ስድስት፡- ልቦለድ--------------------------------------72
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ --------------------------------------72
ክፍል ሁለት፡- መናገር------------------------------------------74
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ------------------------------------------74
ክፍል አራት፡- መጻፍ--------------------------------------------78
ክፍል አምስት፡- ቃላት------------------------------------------78
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው----------------------------------------79
ክፍል ሰባት፡- ሥነ-ጽሁፍ-----------------------------------------81

7 ምዕራፍ ሰባት፡- ሱስ----------------------------------------85
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ -------------------------------------86
ክፍል ሁለት፡- መናገር-------------------------------------87
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ---------------------------------------89
ክፍል አራት፡- መፃፍ-----------------------------------------93
ክፍል አምስት፡- ቃላት---------------------------------------95
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው-------------------------------------96
8 ምዕራፍ ስምንት፡- የግብር አሰባሰብ ምንነትና ጠቀሜታ-99
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ -------------------------------------99
ክፍል ሁለት፡- መናገር-------------------------------------100
ክፍል ሶስት፡- ማንበብ--------------------------------------101
ክፍል አራት፡- መፃፍ----------------------------------------105
ክፍል አምስት፡- ቃላት--------------------------------------106
ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው------------------------------------108
ክፍል ሰባት፡-ሥነ-ጽሁፍ ----------------------------------110

## መግቢያ

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በትምርትነት የሚሰጥበት ዋና ዓላማ የተማሪዎችን የማዳመጥ፣የመናገር፣የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ማጎልበትና የሥነ-ጽሁፍና የስነ- ልሳን እውቀትን ማዳበር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የተማሪዎች መማሪያ መፅሃፍ ነው፡፡ ይህ የስምንተኛ ክፍል መማሪያ መፅሃፍ ሲዘጋጅም የተማሪዎችን እድሜ፣የትምህርት ደረጃ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ችሎታ ያላቸውን ተጋልጦ ታሳቢ አድርጓል፡፡ መፅሃፉ መርሃ ትምህርቱና የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃትን (MLC) በሙሉ እንዲያካትት ጥረት ተደርጓል፡፡ ምንባቦቹ፣ ማብራሪያዎቹና መልመጃዎቹ መርሃ ትምህርቱን መነሻ በማድረግ በክሂልና በእውቀት ዘርፍ ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡

የትምህርት አቀራረቡም ከቋንቋ ክሂሎችና መልመጃዎች የተደራጀ ነው፡፡ ይኸውም ሶስቱን የመማር ዓላማዎች (ግንዛቤ፣አመለካከትና ተግባር) በእያንዳንዱ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ውስጥ ተጨባጭ ሊሆኑ በሚችሉበት መንገድ ተዋቅረው ቀርበዋል፡፡ ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ፅሁፎችና ስዕሎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ምንባቦቹና ማብራሪያዎቹ ግልፅና ሳቢ፣ መልመጃዎቹ ደግሞ በምሳሌ ተደግፈው አሳታፊ ሆነው ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪ ተኮርና አሳታፊ በሆነ ስነ-ዘዴ ላይ በመመስረት ተማሪዎች በግልም ሆነ በጋራ እንዲሰሩና እንዲወያዩ የሚያደርጉ ተግባራትም ተካተዋል፡፡ መምህራንም እንዴት አድርገው ትምህርቱን ማስተማር እንዳለባቸው አቅጣጫ የሚያሳዩ መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ የትምህርቱ አቀራረብ ከቀላል ወደከባድ አካሄድን መሰረት ያደረገ ሲሆን በተማሪዎች መካከል ያለውንየትምህርት አቀባበል ልዩነት፣ የፆታ፣ የባህል፣ የሃይማኖትና የቤተሰብ ኣኗኗርሁኔታ ግምት ውስጥ አስገብቷል፡፡በመጨረሻም ለመፅሃፍ ዝግጅት ፅሁፎቻቸውንያዋሱንን ሁሉ እያመሰገንን፣ስለ መፅሃፉ ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከሌሎችየህብረተሰቡ ክፍሎች የሚቀርቡ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እንገልፃለን፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ሀገር በቀል ዕውቀትና ባህሎች

የምዕራፉ ዋና ዋና ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ሁነቶችን አዳምጣችሁ ምላሽ ትሰጣላችሁ፡፡
- የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ በራሳችሁ አባባል ትገልፃላችሁ፡፡
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺን ትሰጣላችሁ፡፡
- አስረጅ አንቀፅ ትፅፋላችሁ፡፡
- ቁልፍ ቃላትን ትገልፃላችሁ፡፡
- ነጠላና ውስብስብ  አረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ፡፡
- ስለአንድ ታዋቂ ሰው ታሪክ ትፅፋላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡-ማዳመጥ ተግባር

1.መምህራችሁ‹‹የገዳ ስርዓት›› በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን ምንባብ ሲያነቡላችሁ በማዳመጥ የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

ሀ.ሲንቄ ለኦሮሞ ሴቶች የክብር ዘንግ ነች የተባለበት ምክንያት ምንድ ነው?

ለ.በምንባቡ ውስጥ አንዲት ሴት ስታገባ እንደስጦታ የሚበረከትላት ሲንቄ ነው፡፡ለምን?

ሐ.በኦሮሞ ባህል ‹‹ሀደ ሲንቄ›› እና ‹‹አባ ገዳዎች›› እኩል መብት አላቸው? በምሳሌ አብራሩ፡፡

2.ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት በቡድን ተወያይታችሁ ፍቻቸውን አብራሩ፡፡

1. ባህል
2. እርቅ
3. ሚና
4. ግጭት
5. ምኞት

3.ቀጥሎ የቀረቡትን ባዶ ቦታዎች መምህሩ ከሚያነቡላችሁ ምንባብ ውስጥ አሟሉ፡፡

1.የገዳ ሥርዓት የኦሮሞ----------ነው፡፡

2.በገዳ ስርዓት አንዲት ልጅ ስታገባ-----------ይበረከትላታል፡፡

3.-----------በጦርነት መሀል ከገቡ ጦርነቱ ይበርዳል፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር ተግባር


1.ለሚከተሉት ጥያቄዎች በመወያየት መልስ ስጡ፡፡

ሀ. በአዲስ አበባ ከተማ ሰው ሰራሽ ቅርሶች ይገኛሉ?ካሉጥቀሱ፡፡

ለ.በሀገራችን ውስጥ የሚገኙ የምታውቋቸውን ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶችን ከታች የተሰጠውን ስዕላዊ መግለጫ በማየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡









## ክፍል ሶስት ፡- ማንበብ

ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

ሀ.በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ሰው ሰራሽ ቅርሶች ግለጹ፡፡

ለ.ቅርስ ለአንድ ሀገር የሚሰጠው አገልግሎት ምንድን ነው ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ሐ. ይህ ምንባብ ስለምን ጉዳዮች የሚያትት ይመስላችኋል?

# ቅርስ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ተፈጥሮ ያደለቻት እንዲሁም የቀደሙት አባቶቻችን እጅ፣እውቀትና ጥበብ ያረፈበት ተዝቆ የማያልቅ፣ብዙዎችን ያስደነቀ ሀብት አላት፡፡ እነዚህ ሀብቶቻችን ደግሞታሪካችንን፣ባህላችንን፣ወግና ልማዳችንን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፉት ቅርሶቻችን ናቸው፡፡

ቅርስ ሰው ሰራሽና ተፈጠሯዊ በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡ ሰው ሰራሽ ቅርሶች በየዘመኑ ያሉ ሰዎች የፈጠራ ጥበብ ያረፈባቸው ሃውልቶች፣ ለነገስታት መኖሪያነት የታነፁ ግንቦች ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡ተፈጥሯዊ ቅርስ የሚባሉት ደግሞ በተፈጥሮ ድንቅ የሆኑ ቅርሶች ሲሆኑ ከነዚህ መካከል እንጦጦ ይጠቀሳል፡፡ እንጦጦ ከአዲስ አበባ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ከባህርጠለል በላይ 3200 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ እንጦጦ ጥቅጥቅ ባለ ባህር ዛፍ የተሸፈነ ነው፡፡ ለዚህ ይመስላል ሰዎች በተለይም የውጭ ጸሃፍት የአዲስ አበባ ሳንባ የሚሉት፡፡ ደኑ ትንፋሹን ቁልቁል ወደ ውቧ ሸገር እፍ ይልባታል፡፡ እናም በዚህ አይነት የከተማችን ንፁህ አየር ምንጭ እንጦጦ ነው ቢባል ሐሰት አይሆንም፡፡ የእንጦጦ ጫካ ምንጭነቱ ለንፁህ አየር ብቻም አይደለም በከተማችን ዋነኛ የማገዶ መገኛ በመሆኑ የብዙ እናቶች መተዳደሪያ እንዲሁም የብዙዎች መናፈሻ ስፍራ ነው፡፡ ታዲያ እንጦጦን ሳንባ ቢባል ያንስበታል እንጂ ይበዛበታል?




**ጊዜ ምንባብ ጥያቄ፡- የእንጦጦ አቀማመጥ ምን ይመስላል? ካነበባችሁት አንቀፅ ምን ተረዳችሁ?**

እንጦጦ አናት ላይ ከወጡ በአየሩ ይማረካሉ፤ ነፋሻ ነው፡፡ ደኑ አይን ይስባል፤ የአእዋፍ ድምፅ ይመስጣል፡፡ ሁከትና ግርግር የሌለበት ሰላማዊ ስፍራ ነው፡፡ ይህ ስፍራ በውድድር ሜዳ የሃገራቸውን ስም የሚያስጠሩ የብርቅዬ አትሌቶቻችን የስልጠና ስፍራም ጭምር ነው፡፡ ይህ ያጋጠመው ጎብኚ ከነሱ ጋርም የመገናኘት እድል ይገጥመዋል፡፡ እንጦጦ አዲስ አበባን ከዳር እስከዳር ፍንትው አድርጎ ያሳያታል፡፡ አዲስ አበባን ከሚረግጡ ጎብኚዎች በከፍተኛ ደረጃ የሚጎበኝ ስፍራ መሆኑን ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡

ጎብኚዎች እንጦጦ ሲደርሱ የአዲስ አበባን ጓዳ ጎድጓዳ ማየት ይችላሉ፡፡ የሚደረገው ሽርሽር በጣም አስደሳች ነው፡፡ በአካባቢው ያሉ ሰዎችን መመልከት በእጅጉ አስደሳች ነው፡፡ ተራራውን ለመውጣት

45 ደቂቃ ያህል ይወስዳል፡፡
(የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ 2007፡፡ ባህልቱሪዝም፡፡ ገፅ 32-33 መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎ የተወሰደ)

## ተግባር

1.የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልስ ሥጡ፡፡

ሀ. ቅርስ ለአንድ ሀገር የሚኖረው አስተዋፅኦ ምንድነው?

ለ. እንጦጦ ከአዲስ አበባ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ከባህር ጠለል በስንት ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል?

ሐ. ደን ለምን ለምን አገልግሎት ይውላል?

መ. የውጭ ጸሃፍት እንጦጦን የአዲስ አበባ ሳንባ ያሉት ለምን ይመስላችኋል?

ሠ.ከምንባቡ የተረዳችሁትን ዋና ዋና ሀሳቦችን በማንሳት ግለፁ?

2. በምንባቡ መሰረት ቀጥለው ለተዘረዘሩት ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ፍንትው፡- ግልፅ

1.የታነፁ
2.አናት
3.ብርቅዬ
4.መተዳደሪያ
5.ጓዳ ጎድጓዳ
6. ሰው ሰራሽ
7.ቅርስ
8.እውቀት
9. ጎብኚ

3. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች የሚያሟሉ ቃላትና ሐረጎች ከምንባቡ ውስጥ በመፈለግ አሟሉ፡፡

1. ለአዲስ አበባ ከተማ የንፁህ አየር ምንጭ የተባለው……. ነው፡፡
2. .ሀውልቶች ……….ከሚባሉት ቅርሶች የሚመደቡ ናቸው፡፡
3. የእንጦጦን ተራራ ለመውጣት…………ሰዓት ይወስዳል፡፡
4. እንጦጦ ……… ባለ ባህር ዛፍ የተሸፈነ ነው፡፡
5. ……….የሚባሉት በተፈጥሮ ድንቅ የሆኑ ቅርሶች ናቸው፡

## ክፍል አራት፡-መጻፍ

### ማስታወሻ

### አንቀፅ

አንቀፅ ማለት በአንድ ዋና ሀሳብ ላይ ብቻ የሚያተኩር ጽሁፍ ማለት ነው፡፡በአንቀጽ ውስጥ ያለውን ሃሳብ ከሚያብራሩ ዝርዝር ሀሳቦች በስተቀር ሌሎች ሃሳቦች ወይም አጃቢዎች አይጨመሩም፡፡ሰባተኛ ክፍል በአንድ አንቀጽ ውስጥየሚገኙ ኃይለቃል(ዋና)አረፍተ ነገርና ዝርዝር አረፍተ ነገር መሆኑን ተምራችኋል፡፡

### 1.የአንቀጽ ባሕርያት

የአንቀጽ ባህርያት የሚባሉት አንድ አንቀጽ ከሌሎች ጽሁፎች የሚለይባቸውና ሊያሟላቸው የሚገቡ ነገሮች ማለት ነው፡፡ የአንቀጽ ባህርያት የሚባሉት ሦስት ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

### 1 የአንቀጽ አንድነት

በአንቀጽ ውስጥ የሚገኙ አረፍተ ነገሮች በሙሉ በአንድ ሃሳብ ላይ ብቻ ማትኮራቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

### 2.የአንቀጽ ውህደት

በአንቀጽ ውስጥ ያሉት አረፍተ ነገሮች እርስበርስ ያላቸው የጠበቀ ግንኙነት ወይም ትስስርን የሚያመለክት ነው፡፡ በአንቀጽ ውስጥ ያሉ አረፍተ ነገሮች ሲጻፉ እርስበርሳቸው የተያያዙና ፍሰታቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው፡፡

### 3.የአንቀጽ አጽንኦት

በአንቀጽ ውስጥ የሚተላለፈው ሀሳብ ጎልቶ እንዲታይ ለማድረግ የሚቻልበት ስልት ነው፡፡

### ተግባር

1. ቀጥለው ከተሰጡት አንድርዕስ መርጣችሁ ከአርባ ባልበለጡ ቃላት አንድ አንቀጽ ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ቡነ ቀላ

ለ. ባህላዊ ጋብቻ

ሐ. የባህላዊ ምግብ አዘገጃጀት

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

ማስታወሻ

የቃላት ፍች፡- ቃላት አንድን ሃሳብ የሚወክሉ ቢሆኑም እንደሚነገሩበት ማህበራዊ አውድ የተለያየ ፍችን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ይህም ፡-

1. <u>እማሬያዊ ፍች፡-</u> የአንድ ቃል ቀጥተኛ ወይም የመዝገበ ቃላት ፍች ነው፡፡

   ምሳሌ፡- ‹‹ቤት›› የሚለው ቃል ለመኖሪያነትየሚያገለግል ጣሪያና ግድግዳ ያለው ማለት ነው፡፡

   ‹‹ፍየል›› የሚለው ቃል የቤት እንስሳ ማለት ነው፡፡

2. <u>ፍካሬያዊ ፍች፡-</u> የቃላት ምስጢራዊ ወይም ተጨማሪ ፍች ማለት ነው፡፡

   ፍየል የሚለው ቃል ለፍላፊ(ተናጋሪ) ማለት ነው፡፡

2. ለሚከተሉት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. እሳት

ለ. ርግብ

ሐ. እሾህ

መ. ድንጋይ

ሠ. ቀፎ

ረ.ቀበሮ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

ማስታወሻ

መነሻቃል፡- በአንድ ቃል ውስጥ መሰረታዊ ትርጉሙን ይዘው የሚገኙ ድምፃች ቅንጅት መነሻቃል ይባላሉ፡፡ ከመነሻቃል የተለያዩ ቃላትን መመስረት ይቻላል፡፡

መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች፡- ከዋናው ቃል ቀድመው የሚመጡት መነሻ ቅጥያ ሲባሉ ከዋናው ቃል ተከትለው(በኋላ) የሚመጡት የመድረሻ ቅጥያ ይባላሉ፡፡

ምሳሌ፡- ስለተቆጣችው

ስለ- መነሻ ቅጥያ ነው፡፡

ተቆጣ መነሻ(ዋና) ቃል ነው፡፡-ችው መድረሻ ቅጥያ ነው፡፡

### ተግባር

1. ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ቅድመና ድህረ ቅጥያዎችን አውጡ፡፡

| ቃላት | ቅድመ ግንድ | ድህረ ግንድ |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡-አስከበረ | አስ- | - |
| በጎች - | | -ኦች |

1.ስለ መጣ
2. ልጆች
3. በሬው
4. አስተማረችው
5. መለሰች
6. ነገረችው
7. ፍላጎታቸው
8. ምኞታቸው

2. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጡ፡፡

1. በየዋህነት በሚለው ቃል መነሻና መድረሻ ቅጥያዎቹ..... ናቸው፡፡

ሀ. ነ- እና-ት ለ በየ- እና-ት

ሐ. በ- እና -ነት መ. በ- እና-ህነት

2. ላሞች  በሚለው ቃል የመድረሻ ቅጥያው …..ነው፡፡

ሀ -ች ለ. -ሞች ሐ. -ዎች መ. -ኦች

3. ስላገር በሚለው ቃል ዋናው ቃል …….ነው፡፡

ሀ. ገር ለ.አገር ሐ. ላገር መ. ስላገር

4. ግንበኛ በሚለው ቃል የተቀጠለው ቅጥያ ….. ነው፡፡

ሀ.- ኛ ለ. -በኛ ሐ. -ኸኛ መ.-አኛ

5. ከሚከተሉት ቃላት መካካል ቅጥያ የሌለው የቱ ነው?

ሀ. ልጆች ለ. ወንበር

ሐ. ስለመጡ መ. ሄደች

ማስታወሻ

## አረፍተ ነገር

አረፍተ ነገር ማለት ነገር የስማዊና የግሳዊ ሀረግ መዋቅር ነው፡፡ ስማዊ ሀረግ የአረፍተ ነገርን የባለቤት ክፍል የሚያመለክት ሲሆን ግሳዊ ሀረግ ደግሞ የአረፍተ ነገር ማሰሪያ አንቀፅን ያቀፈ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ህፃኑ ልጅ ከትምህርት ቤት መጣ፡፡

በቀረበው አረፍተ ነገር ውስጥ ‹‹ህፃኑ ልጅ›› ስማዊ ሀረግ ሲሆን‹‹ከትምህርት ቤት መጣ›› የሚለው ሀረግ ደግሞ ግሳዊ ሀረግ (የአረፍተ ነገሩ ማሰሪያ አንቀፅ ነው) በዚሁ መሰረት ስማዊ ሀረግ የአረፍተ ነገሩን የባለቤትነት ቦታ ሲይዝ ግሳዊ ሀረግ ደግሞ የማሰሪያ አንቀፁን ቦታ ይይዛል፡፡

የአረፍተ ነገር አይነቶች ሁለት ናቸው፡፡እነሱም፡- ነጠላ አረፍተ ነገር እና ውስብስብ አረፍተ ነገር ናቸው፡፡

ነጠላ አረፍተ ነገር የሚባለው ከአንድ ግስ ብቻ የተመሰረተ አረፍተ ነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡- ጫልቱ ገበያ  ሄደች፡፡

ውስብስብ አረፍተ ነገር የሚባለው ደግሞ በውስጡ ሁለት እና ከዚያ በላይ ግሶችን የያዘ አረፍተ ነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡- አዲስ ሹራብ ስለተገዛልኝ በጣም ተደሰትኩ፡፡  በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ሁለት ግሶች በመኖራቸው ምክንያት አረፍተ ነገሩ ሊወሳሰብ ችሏል፡፡

2. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላና ውስብስብ በማለት ለዩ::
ሀ.እናቴ ልብስ ገዛችልኝ።
ለ.አብዲ እየበላ ያወራል።
ሐ.ፋጡማ ከወንበሩ ላይ ፈጥና ተነሳች።
መ.ጓደኞቻችን ጠዋት ጠዋት ተነስተው ስፖርት ስለሚሰሩ ቀልጣፋዎች ናቸው።
ሠ.ገበሬው ጥሩ ምርት ስላገኘ ደስ አለው።
ረ.ታናሽ እህቴ ባለሞያ ነች።

## ክፍል ሰባት፡-ስነ ፅሁፍ

የግለሰብ የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ

1.ታሪኩ ስለሚፃፍለት ግለሰብ የተፃፉ ፅሁፎችን ማንበብ፣
2.ግለሰቡን የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ የግለሰቡን ትክክለኛ ታሪክ ወይም ማስረጃ መሰብሰብ፣
3.የተሰበሰበውን የግለሰብ ታሪክ በቅደም ተከተል ማደራጀት፣
-ግለሰቡ የተወለዱበትን ቦታ
-የተወለዱበትን ዘመን
-ግለሰቡ የሞቱ ከሆነ የሞቱበትን ዘመን መጥቀስ
-ስለ አስተዳደግ ሁኔታ መግለፅ
-ስለ ትምህርት ደረጃው መጻፍ
-ስለፈጸማቸው ተግባሮችና ስላበረከታቸው አስተዋፅኦዎች ማተት
4.የግለሰቡን ታሪክ ቀላልና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ጽፎ ማቅረብ፣
5. የማስረጃዎችን ምንጭ በተገቢው ቦታ በግርጌ መጥቀስ፣
6.የግለሰቡን ታሪክ የሚያንፀባርቁ ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን በተቀፅላ መልክ ከታሪኩ መጨረሻ ላይ አያያዞ ማቅረብ

## አስቴር ገኖ

የትውልድ ስሟ ገኖ ሳልባና ይባላል፡፡ በ1874 ዓ.ም በጂማ ዞን ሊሙ አካባቢ ተወለደች፡፡ በዘመኑ የነበረው የአካባቢው ሃገር ገዥ በርካታ ህፃናትን በባርነት እንዲ ሸጡ አዘዙ፡፡ በዚህ ትዕዛዝ ከተሸጡት ህፃናት መካከል አንዷ ገኖ ነበረች፡፡ በዚህ ወቅት ዕድሜዋ አስር አመት ነበር፡፡ የመጀመሪያ ገዢዋን ሁለት አመት ካገለገለች በኂላ ለሌላ ሰው ተላለፈች፡፡ ነጋዴዎቹ ወደ አረብ ሃገር ሊያሻግሯት ጥረት እያደረጉ እያሉ በጣሊያን ወታደሮች ቁጥጥር ስር በመዋል እነገኖን ነፃ በማውጣት በአካባቢው ለሚኖሩ የስዊድን ሚሲዮኖች ሰጧቸው፡-፡ ሚሲዮኖች እጅ እንደ ገባች ትምህርቷን ቀጠለች፡፡ የክርስትና እምነትን ከተቀበለች በኂላ አስቴር ገኖ ተብላ ተሰየመች፡፡ አስቴር ገኖ የተለየችሎታ ነበራት፡፡ በተለያዩ ቋንቋዎች የተፃፉትን የእምነት መፅሃፍት ለመተርጎም ተመረጠች፡፡ አስቴር ከህፃንነቷ ጀምሮ ለኦሮሞ ስነ-ጽሁፍ እድገት በተለያዩ መንገዶች አስተዋፅኦ ስታደርግ ቆይታ በ1964 ዓ.ም በ90 አመቷ ነቀምቴ ላይ አረፈች፡፡ ታሪኳ በኦሮሞ ስነ-ጽሁፍና ትምህርት ሁል ጊዜም ሲታውስ ይኖራል፡፡

(ምንጭ፡- ከስምነተኛ ክፍል የተማሪ መፅሃፍ ለማስተማሪያ እንዲሆን ተሻሽሎ የተወሰደ)

### ተግባር

1. ከላይ የቀረበውን የህይወት ታሪክ መሰረት በማድረግ ስለ ክብርት ዶ/ር አበበች ጎበና የሚያዉቁ ሰዎችን ጠይቃችሁ አልያም ከመፀሐፍትና ጋዜጦች ፈልጋችሁ ከህምሳ ቃላት ባልበለጠ አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

የክለሳ ጥያቄዎች

1.ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺያቸውን በዓረፍተ ነገር ውስጥ አስገብታችሁ አሳዩ፡፡

1.እስስት

2. ቀፎ

3. እባብ

4.መሬት

2.በፍካሬያዊ ፍች ቀልጣፋ ወይም ፈጣን የሚለውን ትርጉም የሚሰጠው የትኛው ነው?

ሀ. እሳት ለ. ርግብ ሐ. እርጎ መ. ከበሮ

3.ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ ቅድመና ድህረ ቅጥያዎችን ለዩ፡፡

1.ያመጣችውን

2.ድንጋያማ

3.አስመላሽ

4.ሀገራዊ

5. በሮች

4. የቡድን ውይይት ሲደረግ ከምትከተሏቸው መመሪያዎች ውስጥ ሶስቱን ፃፉ፡፡

1……………………………….

2……………………………….

3……………………………….

# ምዕራፍ ሁለት

## ሳይንስና ቴክሎጂ

የምዕራፉ ዋና ዋና ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ካዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- መረጃን መሰረት በማድረግ አጭር ውይይት ታደርጋላችሁ፡፡
- የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ ትናገራላችሁ፡፡
- የደብዳቤን ምንነት ታስረዳላችሁ፡፡
- የስራ ደብዳቤ ትፅፋላችሁ፡፡
- ለቃላት ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ባዶ ቦታዎችን በተገቢ ቃላት ታሟላላችሁ፡፡

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ተግባር

ማስተወሻ

**ፈሊጣዊ አነጋገር**

ፈሊጣዊ አነጋገር ማለት አንድ ሃሳብ ከተለመደው መደበኛ አገላለፅ በተለየ መልኩ ክብደትና ውበትን ተጎናፅፎ ለአድማጭ እንዲደርስ የሚያደርግ የአነጋገር ስልት ነው፡፡ ፈሊጦች የተናጋሪውን ቋንቋ ውበትና ለዛ በማላበስ የአድማጭን ስሜት የሚኮረኩሩ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- እግረ እርጥብ — እድለኛ

ቀን በቀን — በብርሃን

1.መምህራችሁ ‹‹አያጥበቡ›› በሚል ርዕስ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ ምንባቡን አዳምጣችሁ በውስጡ የተካተቱትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች አውጡና ፍች ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ልብ ገዛ አስተዋለ

ሀ..........................

ለ.........................

ሐ........................

2.የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት››ትክክል ካልሆነ‹‹ሐሰት›› በማለት መልስ ስጡ፡፡

1.የባለታሪኳ አባት አቶ ጥበቡ ናቸው፡፡

2. አቶ ጥበቡ አስተዋይ ሽማግሌ ናቸው፡፡

3. ልጅቷን የሚያስለቅሳት የነበረባት ብሶት ነው፡፡

4. የአቶ ጥበቡ ምክር ልጅቷን የበለጠ አበሳጭቷታል፡፡

5. አቶ ጥበቡና ባለታሪኳ የተገናኙት በመዝናኛ ቦታ ነው፡፡

ክፍል ሁለት፡- መናገር ተግባር

1. የሚከተለውን ጥያቄ በመወያየት መልስ ስጡ፡፡

ሀ. ቡድን መስርታችሁ ‹‹የባህልን›› እና ‹‹የቴክኖሎጂን›› ግንኙነት እንዲሁም ልዩነት ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በቡድን መሪያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ማስታወሻ

## የቡድን ውይይት

የቡድን ውይይት ሲደረግ በቡድን አባላት ሰብሳቢ፣ጸሃፊ፣አቅራቢ፣ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የውይይቱን ሂደት የሚታዘብ ወገን ሊኖር ይችላል። በቡድን ሆናችሁ ስትወያዩ የሚከተሉትን ጉዳዮች ታሳቢ ማድረግ ይጠበቅባችኋል።

- የቡድን አባላት የሚያቀርቡትን ሃሳብ በጥሞና ማዳመጥ
- የሌሎች ቡድኖችን የውይይት ሂደት አለማወክ
- በሚቀርበው ሃሳብ ላይ እንጂ በግለሰቦች ላይ አለማትኮር
- በውውይቱ ውስጥ የላቀ ተሳትፎ ማድረግ
- የቡድናችሁ ድምዳሜ ሲቀርብ እንዳስፈላጊነቱ ማብራሪያ በመስጠት መሳተፍ ናቸው።

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. ቴክኖሎጂ ሲባል ምን ታስታውሳላችሁ ?
2. ቴክኖሎጂ ለአንድ ሀገር እድገት ምን አስተዋጽኦ አለው?
3. ቴክኖሎጂ ለአንድሀገር ምርታማነት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ካላችሁ ልምድ በመነሳት አብራሩ።

## ቴክኖሎጂ

ቴክኖሎጂ ሰው ኑሮውን ለመለወጥ ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገውን ትግልና ከሌሎች የምርት ሃይሎች ጋር በሚፈጥረው ግንኙነት ጉልበትን የሚቀንስና ትርፍ እንዲበዛ ያደርጋል፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ ደግሞየሰውን እንቅስቃሴ በቴክኖሎጂ የተመራ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ቴክኖሎጂ ስንል በተለምዶ ከመሳሪያዎችና ከቁሳቁሶች ጋር የማዛመድ ሁኔታ አለ፡፡ ነገር ግን ቴክኖሎጂ ከመሳሪያዎችና ከቁሳቁሶች በተጨማሪ ከሰው እውቀት፣ከአሰራር ስርዓትና ሂደት እንዲሁም ግንኙነት የሚፈጠር የመረጃ ፍሰት እና ክምችትን አጣምሮ የያዘ ሰፊ ትርጉም ያለው ነው፡፡ በመሆኑም የቴክኖሎጂ አቅም የምርት ሃይሎች የሆኑትን የተፈጥሮ ሃብትና የሰው ሀይል ምርታማነትን ያሳድጋል፡፡ በቴክኖሎጂ አማካኝነት የተፈጠረ ፈጠራ የተሻሻለ ምርትና አገልገሎት፣ የተሻሻለ የአመራረት ሂደት፣ የተሻሻለ የገበያ ልማት ዘዴና የተቋማት አሰራር ሁኔታ ሊሆን ይችላል፡፡

ይህ የቴክኖሎጂ ለውጥ በከፍተኛ መጠን ባለማቋረጥ እያደገ የሚሄድ ጥቅም የሚያስገኝ በምርት ሂደት ውስጥ ግብዓትና የምርት ሀይሎችን አቀናጅ ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ቴክኖሎጂ ለአንድ ሀገር ዕድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው እና ምርት ጨማሪ ነው፡፡ የቴክኖሎጂ ባሕሪይ የቆየ ድህነትና ኋላ ቀርነትን በፍጥነት ለማቃለል፣ የማያቋርጥ ለውጥና እድገትን ለማስመዝገብ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተቀብሎ እየተጠቀሙ መማርና የቴክኖሎጂ ክምችትን እያሳደጉ መሄድ ከአለም አቀፍ የቴክኖሎጂ ፍጥነት ጋር አብሮ ለመሮጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በትምህርትና በምርምር ላይ አመርቂ ስራ መስራት በቴክኖሎጂ ሽግግር ከተቀባይነት አስተሳሰብና ምግባር ባቋራጭ መንጥቆ ሊያወጣን የሚችል መንገድ ነው፡፡ ሆኖም በኢትዮጵያ የምርምር ተቋማት ውጤታማነት አነስተኛ ነው፡፡የዚህም ምክንያት የቴክኖሎጂ ፈጠራ ስርዓት ስላልተዘረጋ ነው፡፡ የሳይንስና

የቴክኖሎጂ ውጤቶች አንቀሳቃሽ ሞተር የሆነ የላቀ እውቀትና ጥረትን የሚሸልም የፉክክር ገበያ መፍጠር ይገባል፡፡
ቴክኖሎጂና ፈጠራን በምርት ሂደቱ ውስጥ ማስተዋወቅ፣ ምርታማነቱን እንዲጨምር ለግል ባለሃብቱ የሚያስገነዝብና የሚያበረታታ የገበያ ስርዓት መገንባት ያስፈልጋል፡፡ በሂደትም የራስን የፈጠራ ስርዓት መገንባት የተማረውን የሰው ሃይል የፈጠራ ባህል በማዳበር ኢኮኖሚውን ከምንጊዜም የእውቀት ጥገኝነት የሚያላቅቅ ነው፡፡ የሰው ሃይሉ የፈጠራ አቅም ማደግና የቴክኖሎጂ ብቃቱ መዳበር በገበያው ውስጥ የተማረ የሰው ሐይል ተፈላጊነቱን ይጨምራል፡፡ ይህም ቁጥሩ በፍጥነት እያደገ የሚገኘውን የተማረ ወጣት የሚጠቅምና ኢኮኖሚውን የሚያሳድግ ይሆናል፡፡

ተግባር

**1.የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል የሆኑትን ‹‹እውነት››ትክክል ያልሆኑትን ‹‹ሐሰት›› በማለት መልስ ስጡ፡፡**

1. በኢትዮጵያ የምርምር ተቋማት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡
2. የሰውን እንቅስቃሴ በቴክኖሎጂ የተመራ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡
3. ቴክኖሎጂ ሲባል ከመሳሪያዎችና ከቁሳቁሶች ጋር የተዛመደ ብቻ ነው፡፡
4. በምንባቡ መሰረት በተቋማት፣በኢንዱስትሪዎችና በገበያው መካከል ያለው ትስስር ደካማ ነው፡፡
5. የራስን የፈጠራ ስርአት መገንባት የተማረውን የሰው ሃይል የፈጠራ ባህል ለማዳበር አስተዋጽኦ አለው፡፡

**2.በምንባቡ መሰረት ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ መርጣችሁ መልሱ፡፡**

1.በቴክኖሎጂ አማካኝነት የተፈጠረ ፈጠራ -------------ሊሆን ይችላል፡፡

ሀ. የተሻለ የአመራረት ሂደት ለ. የተሻለ የገበያ ልማት

ሐ. የተሻለ ምርትና አገልግሎት መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

2. ‹‹የፈጠራ አቅማችንን ለመጠቀም የሄድንበት ርቀት አጭር ነው፡፡›› ሲባል ምን ማለት ነው ?

ሀ. ሙሉ በሙሉ የፈጠራ አቅማችንን ተጠቅመናል፡፡

ለ. የፈጠራ አቅማችን የረቀቀ ነው፡፡

ሐ. የፈጠራ አቅማችንን በጥሩ ሁኔታ አልተጠቀምንበትም፡፡

መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው፡፡

3. ቴክኖሎጂ ቁልፍ ጉዳይ ነው የተባለበት ምክንያት ለምንድነው?

ሀ. ድህነትን በፍጥነት ለማቃለል ስለሚያስችል

ለ. የማያቋርጥ ለውጥና እድገትን ማስመዝገብ ስለሚያስችል

ሐ. ኋላቀርነትን ማቃለል ስለሚያስችል

መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ፡፡

4.ቴክኖሎጂን በተለምዶ ከመሳሪያዎችና ከቁሳቁሶች ጋር የማዛመድ ሁኔታ አለ፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች፡-

ሀ. በምርምር ለ.በዘልማድ

ሐ. ባለማወቅ መ. በታሪክ

5.የምንባቡ አጠቃላይ መልእክት ምን ሊሆን ይችላል?

ሀ.የቴክኖሎጂ አስፈላጊነት

ለ. ቴክኖሎጂ ለምርታማነት ያለው አስተዋጽኦ

ሐ. ሀእና ለ መልስ ናቸው

መ. የግል ባለሃብቶች መበልጸግ

3. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡በ‹‹ሀ›› ረድፍ ያሉትን በ‹‹ለ››ረድፍ ካሉት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1.ባቋራጭ | ሀ. ጎትቶ |
| 2.መንጥቆ | ለ. ትኩስ ሃይል |
| 3. ወጣት | ሐ.ባጭሩ |
| 4. ጠቀሜታ | መ. ጥሩ |
| 5. አመርቂ | ሠ. ገቢ |
| 6. ኢኮኖሚ | ረ. ፋይዳ |
| 7. ስርአት | ሰ. እራሱን ያልቻለ |
| 8.ጥገኝነት | ሸ. ህግ |

**ደብዳቤ**

አንድ ግለሰብ ለሌላ ግለሰብ፣ አንድ ግለሰብ ለመስሪያ ቤት እንዲሁም አንድ መስሪያ ቤት ለሌላ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት የሚጽፈው መረጃ ለማስተላለፍ የሚጠቅም ነው፡፡

**የደብዳቤ ዓይነቶች ሁለት ናቸው፡፡**እነሱም፡-

1. የግል ወይም የዘመድ ደብዳቤ
2. የስራ ወይም የመስሪያ ቤት ደብዳቤ ናቸው፡፡

1. **የዘመድ ደብዳቤ፡-** አንድ ግለሰብ ለሌላ ግለሰብ የሚጽፈው የደብዳቤ አይነት ነው፡፡
2. **የስራደብዳቤ**፡-መስሪያ ቤት ለመስሪያ ቤት፣ መስሪያ ቤት ለድርጅት፣ ድርጅት ለድርጅት እንዲሁም መስሪያ ቤት ለግለሰብ የሚጽፈው የደብዳቤ አይነት ነው፡፡

**የደብዳቤ ክፍሎች**

**አንድ ደብዳቤ ሲጻፍ ሦስት ክፍሎች አሉት፡፡** እነዚህም፡- መግቢያ፣ሐተታና መደምደሚያ ናቸው፡፡

1.**መግቢያ**፡-በዚህ ክፍል የደብዳቤ ቀን፣ ወር፣ ዓ.ም እንዲሁም ሰላምታ ይጻፍበታል፡፡ ደብዳቤው የመስሪያ ቤት ከሆነ ቁጥር፣ ቀን ፣ወር፣ ዓ.ም ፣ የሚጻፍለት መስሪያ ቤት አድራሻና የጉዳዩ ርእስ ይካተትበታል፡፡

2.**ሐተታ**፡-በዚህ ክፍል ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት በዝርዝር ይቀርብበታል፡፡

3. **መደምደሚያ፡-** ከላይ በሐተታ ክፍል የቀረበው ዝርዝር ሀሳብ የሚጠቃለልበት **ክፍልነው**

-------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------
------------------------------------
------------------------------------
------------------------------------

ማስታወሻ

## ስርዓተ ነጥቦች

ስርዓተ ነጥቦች በጽህፈት ጊዜ ሀሳባችን በተሟላና ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲተላለፍ የሚያግዙ ናቸው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ በርካታ ስርዓተ ነጥቦች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት እንመለከታለን፡፡

1. ድርብ ሰረዝ (፤)፡- ተመሳሳይ ሃሳብ ያላቸውን አረፍተ ነገሮች አያይዞ ለማቅረብ የሚያገለግል ስርዓተ ነጥብ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሰዎች ተሰብስበዋል፤ ስብሰባው አልተጀመረም፡፡

2. ነጠብጣብ (…)፡- ተጎርዶ የቀረ ሃሳብ ወይም የተዘለለ ሃሳብ መኖሩን የሚያመለክት ስርዓተ ነጥብ ነው፡፡

   ምሳሌ፡- … ያለበት ዝላይ አይችልም ፡፡

   ልጄ…እናትሽ … ልደፋልሽ፡፡

3. ድርብ ትዕምርተ ጥቅሰ (‹‹ ››)፡- የሚከተሉትን አገልግሎቶች አሉት፡፡

 -ጸሃፊው በጽሁፉ ውስጥ የተጠቀመው ሃሳብ የራሱ ሳይሆን የሌሎች መሆኑን ለማመልከት

   ምሳሌ፡- ‹‹ ድርጅታችን ጨውና ስኳር ያከፋፍላል›› በማለት ስራ አሰኪያጁ አስረዱ፡፡

-የተውሶ ቃላት ሲጠቀም ባዕድነታቸውን ለማመልከት

   ምሳሌ፡- ስልኩ ቀኑን ሙሉ ‹‹ቢዚ›› ነበር፡፡

 -የሁለት ሰዎችን ምልልሳዊ ንግግር እየለዩ ለማሳየት

ምሳሌ፡- ‹‹ መጽሃፉ ተገኘ?››

‹‹ አዎ››

‹‹የት?››

‹‹ ከአልጋው ስር››

4. ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ (‹ ›)፡- ጸሃፊው በጥቅስ ምልክት ውስጥ ባስቀመጠው የሌላሰው ሃሳብ ውስጥ የሌላ ሶስተኛ ሰው ሃሳብ ካጋጠመው ይህንን ሃሳብ ለብቻ ለይቶ የሚያስቀምጥበት ስርዓተ ነጥብ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ‹‹ በርትተን ለመማርና ጥሩ ውጤት ለማምጣት ‹ሁል ጊዜ ትጉ› የሚለውንየመምህራችንን ምክር እናስታውስ›› በማለት የክፍል አለቃው ጓደኞቹን መከረ፡፡

3.ቀጥሎ በቀረበው አንቀፅ ውስጥድርብና ነጠላ ትዕምርተ ጥቅስን በተገቢው ቦታ አስገቡ፡፡

ወይዘሮ ድንቋ ያደገደጉትን ነጠላ አስተካከሉና ይሄ ድግስ ያስፈለገበት ምክንያት ነብሳቸውን ይማርና ፊታውራሪ ለእንደራሴነት ሲወዳደሩ እዚችው ቦታ ነበር ደግሼ ያበላሁት:: ዛሬ ታዲያ አጥናፉ ልጄ ነብስ አውቆ የአባቴ ስም ተቀብሮ አይቅር፤ እኔም ለእንደራሴነት እወዳደራለሁና የቁጭራ ሰፈርተኞችን ደግሰሽ አብይልኝ፡፡እኔ እንኳን የቁጭራ ሰፈርተኞች የአባትህ ውለታ ስላለባቸው ካንተ ሌላ ማንን ይመርጣሉና ድግስ ያስፈልጋል ብዬ ነበር አይሆንም ብሎ አስደገሰኝ እንጂ፡፡

**ክፍል አምስት፡-ቃላት**

ማስታወሻ፡- የቃላት ፍች የአገባብ ፍች እና የመዝገበ ቃላት ፍች በመባል ይታወቃል፡፡ የአገባብ ፍች የሚባለው ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸውን ፍች የሚያሳይ ሲሆን የመዝገበ ቃላት ፍች የሚባለው ደግሞ ቃላት በፊደል ተራ ተደርድረው ፍቻቸውን ከመዝገበ ቃላት ፈልገን የምናገኝበት ነው፡፡

**ተግባር**

1.ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት መዝገበ ቃላት ተጠቅማችሁ ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ምርኩዝ ድጋፍ

ሀ. ሙግት

ለ. መፍትሄ

ሐ. አቻ

መ. ዘለፋ

2.ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ቢፍቱ አመርቂ ውጤት አመጣች፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች‹‹ጥሩ›› የሚለው ይሆናል፡፡

1.መልካም ምግባር በሰዎች ዘንድ ያስመሰግናል፡፡

2. ታታሪ ልጆች ካሰቡት ደረጃ መድረስ ይችላሉ፡፡

3. ለትምህርቱ አጽንኦት የሚሰጥ ተማሪ ደስ ይለኛል፡፡

4. ዘመዴን የመኪና አደጋ ስለጋጠመው ትምህርቱን ለማቋረጥ ተገዷል፡

5.ቅርብ ርቀት መኪና አለመኖሩን ግራና ቀኝን በመቃኘት ማቋረጥ ይገባል፡፡

3. ከሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት መካከል ተገቢ የሆኑትን በመምረጥ አረፍተ ነገሮቹን አሟሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ታሪክ | ሞታለች | የተጨማደደ |
| የተለበለበ | ይገረማሉ | ቀልቤን |
| ሸፍኜ | ቀበጥ | ወደ ውጪ |

ሀ. ዛሬ የምነግራችሁ ተረት ሳይሆን እውነተኛ----------ነው፡፡ለ.

አንድ----------------ልጅ የነበራት አንዲት እናት ነበረች፡፡

ሐ. እናቲቱ ፊቷ--------ነበር፡፡

መ. ሴትዬዋን የሚያዩዋት ሁሉ-------------፡

ሠ. ልጅየው በእናቱ ----------ና የጠቆረ ፊት ያፍር ነበር፡፡

ሬ. ልጅየው ለጓደኞቹ እናቴ------------፤ለሌሎች ደግሞ እናቴ-----------ሀገር ሄዳለች እያለ ይዋሽ ነበር፡፡

ሰ. እናቱ‹‹ አንተን ለማዳን እሳት መካከል-------------ስቼ ገብቼ ነበር አለችው››

ሸ.‹‹አንተን በብርድልብስ-----------አምላኬን እየተማጸንኩ ይዤህ መጣሁ›› አለችው፡፡

የክለሳ ጥያቄዎች

1. ከዚህ በታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

    1. ኦሊያድ ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀመጠ፡፡

    2. በዚህ ዘመን ተሽከርካሪዎች ከፍተኛ አደጋ እያስከተሉ ነው፡፡

    3.ኤቢሲ ከሀገር ሀገር ተሽከርካሪ ነች፡፡

4. አያቴ ወይራ ነው፡፡

5. ወይራ ለቤት መስሪያነት ያገለግላል፡፡

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች ስጡ፡፡

    1. ውህደት

    2. ፈሰገ

    3. ፍላጎት

    4. ነጠረ

    5. ኮረብታ

# ምዕራፍ ሶስት

## ተላላፊ በሽታዎች

1. የምዕራፉ ዋና ዋና ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- ማብራሪያ የሚፈልጉ ጥያቄዎችን አዳምጣችሁ ትመልሳላችሁ፡፡
- ካዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ የወጡ ጥያቄዎች ላይ ትወያያላችሁ፡፡
- ሰፋ ባለ የሚና ጨዋታ ላይ ትሳተፋላችሁ፡፡
- ሰፋ ያለ ጭብጥን ለማውጣት ታነባላችሁ፡፡
- ተዘበራርቀው የተቀመጡ አረፍተ ነገሮችን በማቀናጀት አንቀፅ ትፅፋላችሁ፡፡
- ቃላትን በማጥበቅና በማላላት ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ቃላትን ከተቃራኒ ፍች ጋር ታዛምዳላችሁ፡፡
- የቃል ክፍሎችን ትለያላችሁ፡፡
- የልቦለድ አላባዊያን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ዋናና ንዑስ ገፀ-ባህሪን ትለያላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ቅድመ ማዳመጥ

የሚከተለውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ የምታውቋቸውን በሽታ ተከላካይ ምግቦችና የሚከላከሏቸውን የበሽታ ዓይነቶች ዘርዝሩ፡፡

| የምታውቋቸው በሽታ ተከላካይ ምግቦች | የሚከላከሏቸው የበሽታ ዓይነቶች |
|---|---|
| | |

### የድህረ ማዳመጥ ተግባር

መምህራችሁ በሽታ ተከላካይ በሚል ርዕስ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ምላሻችሁን እርስ በእርስ በመነጋገር በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ነጭ ሽንኩርት ጥሬውን መብላት የሚመረጠው ለምንድነው?
ለ. ሙዝ የደም ግፊትን የሚቀንሰው በምን ምክንያት ነው?
ሐ. ለደም ዝውውር አስፈላጊ የሆነው ነገር የሚገኘው ከየትኛው የምግብ አይነት ነው?
መ. ነጭ ሽንኩርት በምን ያህል ርቀት ላይ ያለን ባክቴሪያን ይገድላል?

## ክፍል ሁለት፡- መናገር ተግባር

1.የሚከተለውን ጥያቄ በቡድን ሆናችሁ ጭውውት አቅርቡ፡፡

ሀ.የኮቪድ መተላለፊያ መንገዶችንና መደረግ ስላለበት ጥንቃቄ የሚያመለክት ስዕላዊ መግለጫውን በመመልከት በጭውውትአቅርቡ፡፡








## ክፍል ሶስት፡-ማንበብ

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. ኮሮና ቫይረስ ምንድነው?
2. የኮሮና ቫይረስ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?
3. ለኮሮና ቫይረስ በሽታ የበለጠ ተጠቂ የሚሆኑት በየትኛው የእድሜ ክልል የሚገኙ ናቸው?

## ኮረና ቫይረስ (ኮቪድ-19)

የኮረና ቫይረስ በሽታ (ኮቪድ-19) ሳርስ -ኮቭ 2 (SARS-COV-2) በተሰኘ ከዚህ ቀደም ተከስቶ በማያውቅ የኮሮና ቫይረስ ዝርያ የሚመጣ የመተንፈስ ችግር የሚያስከትል ተላላፊ በሽታ ነው፡፡ ሳርስ ኮቭ-2 በመባል የሚታወቀው ይህ ቫይረስ ከኮሮና ቫይረስ ዝርያ ቤተሰብ አንዱ ነው፡፡



ቫይረሱ ከሌሊት ወፍ ከሚገኘው ሳርስ ኮሮና ቫይረስ ጋር ካለው የ96በመቶ ቀረቤታ አንፃር ከሌሊት ወፍ የመጣ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ቫይረሱ ወደሰው ከመተላለፉ በፊት ሌሎች እንስሳቶች እንደ መካከለኛ (የቫይረሱ) አስተላላፊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ቫይረስ በእንስሳት ውስጥ

ከመተንፈሻ በሽታነት በተጨማሪ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች ላይ በሽታን ያስከትላል፡፡ ይሁንና በሰዎች ውስጥ ከቀላል እስከ ከባድ የመተንፈሻ አካላት ህመም ያሉ በሽታዎችን የሚያስከትል ነው፡፡ ሌሎች የኮሮና ቫይረስ አይነቶች ውስጥ ሳርስ ኮቭ(SARS COV) እና መርስ ኮቭ(MERS-COV) በመባል የሚታወቁ ቫይረሶች ይገኙበታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ እነዚህ ቫይረሶች ሳርስ በ2002 እ.ኤ.አ እና መርስ በ2012 እ.ኤ.አ ብዙ ሰዎችን የያዘ ወረርሺኝ አስከትለው አልፈዋል

ለመጀመሪያ ጊዜ ከውሃን ከተማ ሁቤይ ክፍለ ሀገር ቻይና መንስዔው ያልታወቀ የሳንባ ምች ህሙማን እንደነበራቸው በታህሳስ 21/2012 ዓ.ም ለዓለም ጤና ድርጅት አሳውቀዋል፡፡ ይሁንና ቫይረሱ ከቻይና አልፎ ሌሎች ሀገራት ላይ በፍጥነት እየተስፋፋ ብዙ ሰዎች ከመያዛቸውም በላይ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ህይወት ቀጥፏል፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ የአለም ጤና ድርጅት በሽታው በዓለም አቀፍ ደረጃ ለህብረተሰብ ጤና አሳሳቢ ችግር መሆኑን በጥር 21/2012 ዓ.ም አውጇል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቫይረሱ በብዙ ሀገራት ውስጥ በመሰራጨቱና ብዙ ህዝብን በመያዙ የዓለም የጤና ድርጅት መጋቢት 2/2012 ዓ.ም በሽታውን የዓለም ወረርሺኝ (Pandemic) እንደሆነ አውጇል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከጥር 18/2012 ዓ.ም ጀምሮ ለኮቪድ -19 የድንገተኛ ጊዜ ዝግጅትና ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል በማቋቋም ለበሽታው ቁጥጥር ውጤታማነት የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ዝግጅት ስታደርግ ቆይታ የመጀመሪያውን በበሽታ መያዙ የተረጋገጠ ሰው በመጋቢት 3/2012 ዓ.ም ሪፖርት ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም በዓለም ዙሪያ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ህይወት የቀጠፈው ኮሮና ቫይረስ በእናቶች እና ህፃናት ጤና ላይ ተጨማሪ ስጋቶች ማስከተሉን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አስታውቀዋል፡፡ በወረርሽኙ ምክንያት ለእናቶችና ህፃናት የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች 20 በመቶ በመቀነሳቸው የእናቶች ልጅ የመውለድ እና የታዳጊ ህፃናት ሞት ጨምሯል፡፡

(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ አዲስ አበባ (2012፡፡)

## ተግባር

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆኑትን‹‹እውነት››ስህተት የሆኑትን‹‹ሀሰት›› በማለት መልስስጡ።

1.ኮሮና ቫይረስ የበለጠ በእናቶች እና በህጻናት ጤና ላይ ስጋት አስከትሏል።

2. በሀገራችን በኢትዮጵያ የኮሮና ቫይረስ የመጀመሪያው ተጠቂ ሰው

የተረጋገጠው መጋቢት 2/2012 ነው።

3. የኮሮና ቫይረስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተው በቻይና ሁቤይ ክፍለ ሀገር ነው።

4 .ከዚህ ቀደም ሳርስ ኮቭ እና ማርስ ኮቭ ብዙ ሰዎችን የያዘ ወረርሽኝ አስከትለው አልፈዋል።

5 .ኮሮና ቫይረስ ከባድ የመተንፈሻ አካል ህመም ያስከትላል? ምክንያታችሁን ግለጹ ።

6. እንስሳቶች እንደ መካከለኛ የቫይረሱ አስተላላፊ ሊሆኑ ይችላሉ? እንዴት?

2. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላት ፍች ስጡ፡፡

ሀ. ታዳጊ
ለ. ወረርሽኝ
ሐ. የተረጋገጠ
መ. እርምጃ
ሠ. ቀጥፏል
ረ. መሰራጨት
ሰ. ማዕከል
ሸ. ቀረቤታ

ክፍል አራት፡- መጻፍ

ተግባር

1.ቀጥለው ተዘበራርቀው የቀረቡ አረፍተ ነገሮች አሉ፡፡ ጅምሩን መሰረት አድርጋችሁ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቃችሁ ጨርሱ፡፡

ሀ. ከዚያም በየስፍራው በጀግንነት ሲዋጉ ቆስለው ተማረኩ፡፡
ለ. ፋሽስቶችም ብዙ ካጉላሏቸው በኋላ ወደ ኢጣሊያ ሀገር ወሰዷቸው፡፡
ሐ. ሀገራችን በፋሽስት ጣሊያን ስትወረር በወለጋ በኩል የመጣውን ጠላት ለመመለስ ከሌሎች አርበኞች ጋር ዘመቱ፡፡
መ. ሌተናል ኮሎኔል አብዲሳ አጋ በቀድሞ ወለጋ ክፍለ ሀገር ነጆ ወረዳ ኪዳነ ምህረት በተባለ አካባቢ ተወለዱ፡፡
ሠ. ከዚያም ገነት ጦር ት/ቤት ገብተው በውትድርና ሙያ ሰለጠኑ፡፡

ሌተናል ኮሎኔል አብዲሳ አጋ በቀድሞ ወለጋ ክፍለ ሀገር ነጆ ወረዳ ኪዳነ ምህረት በተባለ አካባቢ ተወለዱ፡፡

------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ተግባር

1. ለሚከተሉት ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚኖራቸውን ፍች ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ለጋ ሲጠብቅ ‹‹መታ›› ሲሆን፣ላልቶ ሲነበብ ያልደረሰ፣ያልበሰለ (ጮርቃ) ማለት ነው፡፡

1. ገና
2. ዋና
3. ሰባ
4. ሰፊ
5. ጥሬ
6. አያት
7. ጠላት
8. አባይ
9. ሽፍታ
10. ይጠብቃል

2. በ‹‹ሀ›› ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት ከ‹‹ለ›› ረድፍ ከተዘረዘሩት ተቃራኒያቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ግልፅ | ሀ.ጥቂት |
| 2. ብዙሃን | ለ. ስውር |
| 3. ግቢ | ሐ.ፅዱ |
| 4. ቆሻሻ | መ.ግዴታ |
| 5. መብት | ሠ.ውጪ |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

ማስታወሻ

የቃል ክፍሎች

1.ስም፡- ከቃላት ክፍሎች አንዱ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የሚመደቡት እንደ ቤት፣ ላም፣ ልጅ፣ በግ ወዘተ ላሉ ነገሮች መጠሪያ ሊሆኑ የሚችሉ ነፃ ምዕላዶች ወይም ቃላት ናቸው፡፡

2.ቅፅል፡- የነገሮችን ባህርይ፣ቅርፅ፣መጠን፣ቀለም፣ወገን ወዘተ የሚገልፅ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ጥሩ - ባህርይን የሚገልፅ

ትንሽ - መጠንን የሚገልፅ

ክብ - ቅርፅን የሚገልፅ

ቀይ - ቀለምን የሚገልፅ

ኢትዮጵያዊ - ዜግነትን የሚገልፅ

3.ግስ፡- ድርጊትን ወይም ሁነትን የሚያመለክት ማሰሪያ አንቀፅ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሰበረ ፣ ገደለ፣ወሰደ

4.ተውሳከ ግስ፡- በግዕዝ ተውሳከ ማለት ተጨማሪ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ተውሳከ ግስ የግስ ጭማሪ ማለት ነው፡፡ ከግስ ጋር እየገቡ ግሱ የሚገልፀው ድርጊት እንዴት፣ መቼ፣ ለምን፣ በምን ሁኔታ እንደተፈፀመ ይገልፃሉ፡፡

ምሳሌ፡- ገና፣ ቶሎ፣ክፉኛ፣ ምንኛ፣አሁን ናቸው፡፡

5.መስተዋድድ፡- የሚለው ቃል ትርጉም የሚያዋድድ ማለት ነው፡፡ አንድን ቃል ከሌላ ቃል ጋር ያዛምዳል ወይም ያዋድዳል፡፡

ምሳሌ፡- ስለ፣ እንደ፣ ወደ፣እስከ

(ምንጭ፡-ባየ ይማም፣ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው ( 2010)

## ተግባር

1. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በየቃል ክፍሎቻቸው መድቡ፡፡
   1. ዘወትር
   2. ደበቀ
   3. ጥቁር
   4. ወደ
   5. ከ
   6. ኪስ
   7. ፍርሃት
   8. ግምኛ
   9. ደነገጠ
   10. ደግ
2. በሳጥኑ ውስጥ የተዘረዘሩትን ቃላት መርጣችሁ ባዶ ቦታዎችን አሟሉ፡፡

| | |
|---|---|
| ከብቶቹ | ጠቆሙ |
| -ለ | መጥፎ |
| ደጋግሜ | |

1.ፈተናውን ለማለፍ -------------አጠናሁ፡፡

2.---------------ሽታ ለጉንፋን ያጋልጣል፡፡

3. ጠባቂዎቹ የአጭበርባሪዎቹን አድራሻ-------------፡፡

4. ቢሊሴ ---------------ተቸገሩ ቤተሰቦቿ ደራሽ ናት፡፡

5. -----------------ወደ በረታቸው ገቡ፡፡

## ክፍል ሰባት፡- ስነ-ጽሁፍ

### የልቦለድ አላባውያን ( ፍሬ ነገሮች)

1.ታሪክ፡- በተወሰነ የጊዜ ቅደም ተከተል የተቀናጁ ሁነቶች ትረካ ነው፡፡

2.ትልም፡-የሁነቶች ትረካ ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱ ግን በምክንያትና ውጤት ላይ ነው፡፡

3.ገፀ-ባህርይ፡- በልቦለድ አለም ስጋ ለብሰው፣ መጠሪያ ተሰጥቷቸው፣ የሚንቀሳቀሱ፣ የሚተነፍሱ፣ የሚናገሩ ወዘተ እንደ እውኑ አለም ሰዎች የሚኖሩ፣ የሚሞቱ፣ የሚርባቸውወዘተ የልቦለድ አለም ሰዎች ናቸው፡፡ ገፀ-ባህርይ በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፡-

ሀ. ዋና ገፀ- ባህርይ፡- ማለት በልቦለድ ታሪክ ውስጥ ዋና ባለታሪኮች ሆነው ከታሪኩ ጅማሬ እስከ ፍፃሜው የሚጓዙ ናቸው፡፡

ለ.ንዑስ ገፀ-ባህርይ፡- ማለት የልቦለዱ ታሪክ በመተረክ ላይ እያለ በመሃል እየገቡ ወይም ወጣ ገባ እያሉ ዋናውን ገፀ-ባህርይ የሚያጅቡ ናቸው፡፡

4.ግጭት፡- በልቦለድ አለም የሚኖሩ ገፀ- ባህርያት በተፈጠረላቸው እርስ በእርሳዊ ግንኙነት የተነሳ በተለያዩ ምክንያቶች ቅራኔዎች ወይም አለመግባባቶች ውስጥ ይገባሉ፡፡ በነዚህ ቅራኔዎች ወይም አለመግባባቶች ሳቢያ የሚፈጠረው ፍልሚያ ግጭት ይባላል፡፡

5.መቼት፡- የልቦለድ ገፀ-ባህርያት የሚኖሩበትንና ታሪካቸውን የተከናወነበት ጊዜና ቦታን የሚያመለክት ነው፡፡

6.ጭብጥ፡- ልቦለድ የሚፃፍበት ዓይነተኛ አላማ ወይም የልቦለድ ጽሁፍ አጠቃላይ መልዕክት ነው፡፡

7.አንፃር፡- ደራሲው የልቦለዱን ታሪክ የሚያቀርብበት የትረካ አቅጣጫ ነው፡፡

(ምንጭ፡-ዘሪሁን አስፋው፣የስነ-ጽሁፍ መሰረታውያን(2007)

## ተግባር

1. ቀጥሎ ከቀረበው የልቦለድ ቅንጫቢ ውስጥ ዋናና ንዑስ ገጸ-ባህርይን ለዩ።

… ‹‹እንዲሁም።›› አለ ጉዱ ካሳ አይኑን ከበዛብህ ላይ አንስቶ በር በሩን እየተመለከተ። ‹‹እንዲሁም አንድ የድሃ ልጅና አንዲት የጌታ ልጅ ቢዋደዱና ሊጋቡ ቢፈልጉ የድሃው ልጅ ያለአቅሙ ተንጠራራ ብለው ያሽሟጥጡኛል ብሎ ይሰጋል። የጌታዋ ልጅም በበኩሏ ማዕረጓን አልጠበቀችም እባላለሁ ብላ ትፈራለች። ለወዳጇ ያላት ፍቅር ይሉኝታዋን የሚያሸንፍ ቢሆን እንኳን ወላጆቿ ስለማይፈቅዱላት አዝና አልቅሳ አንጀቷ ተቆርጦ የምትወደውን ሳታገባ ትቀራለች!›› አለና ጉዱ ካሳ እበሩ ላይ አርፎ የነበረውን አይኑን መልሶ በዛብህ ላይ ተክሎ ፍጥጥ አድርጎ ያየው ጀመር።

በዛብህ ጉዱ ካሳ በመጨረሻ የተናገረው ስለሱና ስለ ሰብለ መሆኑን ጠርጠሮ ልቡ እንደ መሸበር አለና አንገቱን እንደ ደፋ እጁን በእንጀራ ይጠራርግ ጀመር።

‹‹ ታዲያስ እውነት አይደለም?›› አለ ጉዱ ካሳም እጁን በእንጀራ እየጠራረገ።

‹‹ምኑ?›› አለ በዛብህ ቀና ብሎ። ከመደንገጡ የተነሳ በግምባሩ ላይ ይታይበት ነበር።

‹‹አሁን ያልኩት ሁሉ እውነት አይደለም?››

‹‹ይሆናል እንጃ ይሆናል!››

‹‹አንተና ሰብለም ያላችሁበት ሁኔታ ይህን የመሰለ ነው!››

‹‹ሞ…ሞ…ምንድነው እኔና ሰብለ ያ…ያለንበት?›› አለ በዛብህ ብርቱ ብርድ አንጀቱ ውስጥ እንደገባ እየጠንቀጠቀጠ።

ምንጭ ፡- አዲስ አለማየሁ (1958) ፍቅር እስከ መቃብር

የክለሳ ጥያቄዎች

ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉ ቃላትን በየቃል ክፍላቸው ለይታችሁ አስቀምጡ፡፡

1. ገበሬው መሬቱን ቆፈረ፡፡
2. ነጋዴው ገንዘቡን ባንክ አስቀመጠ፡፡
3. ፊራፊስ ከአዲስ  አበባ ወደ ወለጋ በመኪና ሄደ፡፡
4. ሲንቦ የአማርኛ መፅሀፍ ስለጠፋባት ክፉኛ አለቀሰች፡፡

ለ. በመጥበቅና በመላላት የትርጉም ለውጥ እንዲያመጡ ያደረገውን ድምፅ ለይታችሁ አውጡ፡፡

1. ቁርስ
2. በሽታ
3. አነባለሁ
4. በሬ
5. አካፋ

ሐ. ያነበብኩት ልቦለድ ገጸባህርያቱ ከተለያዩ የህይወት አቅጣጫዎች አንጻር <u>የተሳሉ</u> ናቸው፡፡

የተሰመረበት ቃል ፍች -------ነው፡፡

ሀ.የተሞረዱ    ለ.የተፈጠሩ

ሐ. የተገለሉ   መ. መልስ የለም

# ምዕራፍ አራት

## ግጥም

የምዕራፉ ዋና ዋና ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ሰፋ ያለ ማብረሪያ የሚፈልጉ ጥያቄዎችን አዳምጣችሁ በቃል ትመልሳላችሁ፡፡
- በተወያያችሁት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ትናገራላችሁ፡፡
- አጭር ታሪኮችና ግጥሞችን ለተዝናኖት ታነባላችሁ፡፡
- አያያዦችንና መስተዋድዶችን ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገሮችን ታዋቅራላችሁ፡፡
- ተውላጠ ስምና ባለቤትን ትለያላችሁ፡፡
- ጅምር ስንኞችን ትቋጫላችሁ፡፡
- ተዘበራርቀው የተቀመጡ ግጥሞችን አስተካክላችሁ ትፅፋላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ተግባር

1.መምህራችሁ‹‹ሁለት መላጦች›› በሚል ርዕስ የሚያነቡላችሁን ግጥም በትክክል አዳምጣችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ሁለቱ ሰዎች የተሸቀዳደሙት ለምንድነው?
2. ‹‹ሁለት መላጦች›› እና ‹‹ሁለት በራ ሰዎች›› የሚሉት ሐረጋት ልዩነት አላቸው? ምክንያቱስ ምንድነው?
3. አንደኛው ሰው እቃውን የወሰደው በምን አይነት ሁኔታ ነው?
4. የተገኘው እቃ ለሁለቱም ሰዎች ያገለግላል? ምክንያታችሁ ምንድነው?
5. አገላበጠና ቢመለከት ፈጥኖ፣ እቃውን አገኘው ማበጠሪያ ሆኖ፡፡ በነዚህ ስንኞች ውስጥ ቤት መድፊያው ቃል የትኛው ነው?
6. ያዳመጣችሁት ግጥም መልዕክት ምንድነው?

2.ያዳመጣችሁትን ግጥም መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በቃል ፍች ስጡ፡፡

ሀ. ሚዶ
ለ. ተሯካከሩ
ሐ. ፈጥኖ
መ. ጎዳና
ሠ. በራ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር

1.የሚከተሉትን አጫጭር ቃላዊ ግጥሞች በቡድን ሆናችሁ በይዘቱ ላይ በመነጋገር የብሶት፣ የፍቅር፣ የሙገሳና የስራ በማለት ለይታችሁ ተናገሩ፡፡

ሀ. ከሳሽን ጠቆርሽን ይለኛል ባላገር፣
 የሆዴን አውጥቼ ለስንቱ ልናገር፡፡
ለ. አንድ እንጀራ እራቴ መስተዋቴ ነሽ፣
 ከቶ የስንቱን ፊት ታሳይኛለሽ፡፡
ሐ. በሬና ገበሬ ቢጣሉም አይበጅ፣
 እንዲያ ሰተትብሎ ይጠመዳል እንጅ፡፡
መ. አስራ ሁለት ሆነን አንድ ሰው ወደን፣
 እሷ ትስቃለች እኛ ተጨንቀን፡፡
ሠ. የጎበዝ እናት ታስታውቃለች፣
 አፋፍ ላይቆማ በለው ትላለች፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ግጥም ምንድነው?
2. በግጥም ውስጥ ቤት የሚባለው ምንድነው?
3. ቤት መምቻና ቤት መድፊያ ልዩነታቸው ምንድነው?

## ደግነትና ክፋት

አንድ ሰው ነበረ ቅንነትን ወዳድ፣
ለሁሉ ማዘንን አድርጎ እንደ ልማድ፣
ይኖር የነበረ ነቅቶ እንደ ዘበኛ፣
ደግ ስራ ለመስራት ልቦናው ሳይተኛ፡፡

አንድ ቀን ማለዳ ተነስቶ ሲሄድ፣

እባብ ወድቆ አገኘ ከመሀል መንገድ፣
አመዳይ ጥሎበት ውርጭ አቆራምዶት፣
አስራ አምስት ደቂቃ የቀረው ሊሞት፣
ሰውዬውም አዝኖ ይሄን በማየት፣
ከመሬት አንስቶ በእጁ ጨብጦት፣
ከቤቱ አገባና በድኑን እባብ፣
ዘርግቶ አስቀመጠው ምድጃ አጠገብ፡፡
እሳት እያሞቀ ጥቂት እንዳቆየው፣
እጥፍ ዘርጋ እያለ ሲንቀሳቀስ አየው፡፡
ሁለንተናው ሞቆ ህይወት ሲሰማው፣
ተንኮልና ቁጣ አንድነት ሆነው፣
የተፈጥሮው ክፋት በልቦናው መጥቶ፣
የሚነክሰው ሲሻ  ምላሱን አውጥቶ፣
ሞቶ የነበረ የበድን እሬሳ፣
ያዳነውን ሊነድፍ እራሱን አነሳ፣
ሰውዬውም አይቶ ይህን አኳኋኑን፣
በሰራው ደግነት አዘነ በውን፣
ምንም ክፋት ለሱ ገንዘቡ ባይሆን፣

ደጉን ክፉ አድራጊ የተገባ ቁጣ፣
እንደ እሳት ተፋጅቶ በልቡ ላይ መጣ፣
መጥረቢያ አነሳና እባቡን ቢለው ፣
ካራት ላይ ቆርጦ በጣጥሶ ጣለው፡፡
ሰው ደግ ሲውልለት እባብ እየከዳ፣
በደግ አድራጊው ላይ መርዙን አሰናዳ፡፡
ክፉም ሰው እንደዚህ የክፋቱ ክፋት፣
ደግ የዋለለትን ያስባል ለማጥፋት፣
ተንኮሉም ባሰበው መንገድ መሄድ ትቶ፣
የገዛ ጥፋቱን ያመጣል ጎትቶ፡፡
(ምንጭ፡- ከበደ ሚካኤል(1999)፣ የቅኔ ውበት ፣ገፅ 21-22)

## ተግባር

1. ያነበባችሁትን ግጥም መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ከቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጡ፡፡

1.የግጥሙ አራተኛ ስንኝ መነሻ ሀረግ የትኛው ነው? ሀ. ደግ ስራ ለ. ደግ ስራ ለመስራት ሐ. ተነስቶ ሲሄድ መ. አንድ ቀን ማለዳ

2. አራተኛው አንጓ ስንት ስንኞች አሉት?

ሀ.13 ለ.9 ሐ.16 መ.14

3. የመጨረሻዎቹ ተከታታይ ሁለት ስንኞች ቤት ….ነው፡፡

ሀ. ኦ ለ. ቶ ሐ. ት መ. ጎ

4. ከላይ የቀረበውን ግጥም ከሚከተሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች በየትኛው ማጠቃለል ይቻላል?

ሀ. ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ።

ለ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች።

ሐ. እህል ላበደረ አፈር፣ ወርቅ ላበደረ ጠጠር።

መ. ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል።

5.ገጣሚው ለተደራሲያን ለማስተላለፍ ከፈለገው መልዕክት መካከል ልዩ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ.ከክፋት ደግነት ይሻላል። ለ. መልካምነት ጥሩ ነው።

ሐ. የወደቀን ማንሳት ያስመሰግናል። መ. ክፉ ለሰራምላሹ ምስጋና ነው።

2. ቀጥለው የቀረቡት ቃላት ከግጥሙ የወጡ ናቸው። በግጥሙ መሰረት ፍቺያቸውን አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ውርጭ | ሀ. ህብረት |
| 2. ህይወት | ለ. መልካምነት |
| 3. አንድነት | ሐ. አዘጋጀ |
| 4. በድን | መ. ብርድ |
| 5. ሲሻ | ሠ. እስትንፋስ ያለው |
| 6. አሰናዳ | ረ. የማይንቀሳቀስ |
| 7. ቅንነት | ሰ. ሲፈልግ |

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

ማስታወሻ

አያያዥ ቃላት፡- ማለት ቃልን ከቃል፣ ሀረግን ከሀረግ፣አረፍተ ነገርን ከአረፍተ ነገር የሚያጣምር ወይም የሚያይዝ ነው፡፡ አያያዥ ቃላት የተለያየ አገልግሎት አላቸው፡፡ ከዚህም አገልግሎት አንፃር በተለያየ ክፍል ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፡-

1. ውጤትን አመልካች አያያዥ ቃላት፡-
እነዚህ አያያዥ ቃላት በአንድ ነገር መከሰት ምክንያት የሚመጡ ውጤቶችን ለማመልከት የሚረዱ ናቸው፡፡
ምሳሌ፡- ትምህርቱን በደንብ ያጠናል፤ ስለዚህ ጥሩ ውጤት ያመጣል፡፡

2. አማራጭ ወይም አጠራጣሪ አያያዥ ቃላት፡-
እነዚህ አያያዥ ቃላት ከቀረቡ ነገሮች አንዱን ለመምረጥ አጠራጣሪ ነገሮች ሲከሰቱ አማራጮችን ለማስቀመጥ ይጠቅማሉ፡፡
ምሳሌ፡- ኬክ ወይስ ብስኩት ይገዛልሽ ?

3. አፍራሽ ወይም ተቃራኒ ሃሳቦችን አያያዥ ቃላት ፡-
እነዚህ አያያዥ ቃላት በሃሳብ የሚቃረኑ ነገሮችን ለማያያዝ ይጠቅማሉ፡፡
ምሳሌ፡- ቅርጫት ኳስ እወዳለሁ፤ ግን ከእግር ኳስ አይበልጥም፡፡

4. ተጨማሪ ሃሳቦችን ለማያያዝ የሚጠቅሙ አያያዥ ቃላት፡-
እነዚህ አያያዥ ቃላት ከአንድ ሃሳብ በኋላ ተጨማሪ ሃሳብ መኖሩን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- ወሬ አልፈልግም አልኩህ እንግዲህ አርፈህ ተቀመጥ፡፡

## ተግባር

1. የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት ተጠቅማችሁ ተከታዩን አንቀፅ አሟሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ስለሆነም | ሆኖም | ይሆን |
| እንዲሁም | ወይም | ና |
| ስለዚህ | ከዚያም | ሳይሆን |
| ደግሞ | | |

ቁጠባ ከዕለት ተዕለት ፍጆታችን በማብቃቃት ለወደፊት ዕቅዶቻችን ማሳኪያ ___ሀ___ዘንድ የሚቀመጥ ገንዘብ ማለት ነው፡፡የወደፊት ዕቅዶቻችን___ለ___ ድንገት ደራሽ ጉዳዮች ሁል ጊዜ ተርፎን ባስቀመጥነው የገንዘብ መጠን የማይመለሱ ___ሐ___ የማይገዙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ___መ___ቁጠባ ሲተርፈን የምናደርገው ___ሠ___ ከምናገኘው ና ካለን ላይ በመቀነስ የምናስቀምጠው ገንዘብ ነው፡፡ በርካቶች ‹‹አሁን ለኑሮዬ የሚያስፈልጉኝ ነገሮች መግዛት ካልቻልኩ ለወደ ፊቱ መቆጠብ ለምን ያስፈልገኛል›› ሌሎች ___ረ___ ‹‹ያልተረፈኝን ገንዘብ አብቃቅቼ የምቆጥበው ለምንድ ነው›› ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡እነዚህን ጥያቄዎች የሚመልሱ ___ሰ___ ቁጠባን የህይወታችንና የኑሯችን አካል እንድናደርግ የሚያስገድዱን በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡

## ክፍል አምስት ቃላት

### ተግባር

1. ከሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. የተናደደ ሰው ስህተት ይፈፅማል፡፡
2. ፖሊሱ ሌባውን ከግቢው ላይ አነቀው፡፡
3. አሳቻ ስፍራ ላይ ጠብቀው ድንገተኛ አደጋ አደረሱበት፡፡
4. ንግግሩ በፌዝ የተሞላ ነበር፡፡
5. አሳ ለማስገር ወደ ሃይቅ ወረደ፡፡
6. የስራው ውጥን ያስደስታል፡፡
7. በሙዚቃ መሳሪያ አጨዋወት የተካነ ነው፡፡
8. ሙሽሮቹ ታጅበው ከቤት ወጡ፡፡
9. ከጥንካሬያቸው ብዙ ሊያካፍሉን የሚችሉ ሴቶች እንዳሉ መታወቅ ይኖርበታል፡፡
10. ቤቱ በጥራት ስላልተሰራ ተናደ፡፡

2.ቀጥለው የቀረቡትን ቃላት ቀጥተኛ ፍቻቸውን ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| 1.ማወደስ | 6. ተማፀነ |
| 2. ዝንባሌ | 7.ብላቴና |
| 3.ጥንድ | 8.ባዝራ |
| 4.አማላይ | 9.አመነታ |
| 5. ማዕበል | 10.የወል |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

ማስታወሻ

ተወላጠ ስም፡- ማለት የስም ምትክ ወይም ልዋጭ ማለት ነው፡፡ ስምን እየደጋገመ ከመጥራት እኔ፣እኛ፣አንተ፣አንቺ፣ እናንተ፣እሱ፣እሷ፣እነሱ እያሉ በመተካት ማሳጠር ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ሮቤራ በማለት ፋንታ እሱ ብሎ ስለ ሮቤራ መናገር ይቻላል፡፡ ስለዚህም ተውላጠ ስሞች የስም ልዋጭ ስለሆኑ ስም በሚለው የቃል ክፍል ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ተውላጠ ስሞች በሶስት ምድብ ማየት ይቻላል፡፡

| ቁጥር | መደብ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 1ኛ | 2ኛ | | 3ኛ | |
| | | ተባዕት | እንስት | ተባዕት | እንስት |
| ነጠላ | እኔ | አንተ | አንቺ | እሱ | እሷ |
| ብዙ | እኛ | እናንተ | | እነሱ | |

ተግባር

1.ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሰረት አሟሉ።

| ተ.ቁ | ግስ | እኔ | እኛ | አንተ | አንቺ | እናንተ | እሷ | እሱ | እነሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰበረ | ሰበርኩ | ሰበርን | ሰበርክ | ሰበርሽ | ሰበራችሁ | ሰበረች | ሰበረ | ሰበሩ |
| 2 | ወረደ | | | | | | | | |
| 3 | ጠጣ | | | | | | | | |
| 4 | ሄደ | | | | | | | | |
| 5 | መጣ | | | | | | | | |
| 6 | ወሰደ | | | | | | | | |
| 7 | ፈለጠ | | | | | | | | |
| 8 | ከመረ | | | | | | | | |
| 9 | አወረደ | | | | | | | | |
| 10 | ደረሰ | | | | | | | | |

2. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ባለቤት አመልካች ቅጥያዎችን ከግሶቹ ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

ምሳሌ፡- ነኢማ ደብዳቤ ፃፈች፡፡ ‹‹ፃፈች›› በሚለው ግስ ላይ ‹‹-ች›› ባለቤት አመልካች ቅጥያ ነች፡፡ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ነኢማ ( እሷ) መሆኑን ያሳየናል፡፡

ሀ.ናኦል ጥፋት ስላጠፋ ተገረፈ፡፡

ለ. ሚልኪ በጥዋት ስፖርት ስትሰራ ወደቀች፡፡

ሐ. እንግዶቹ ተስተናግደው ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡

መ. እሷ አትክልት ለመግዛት ወደ ገበያ ሄደች፡፡

ሠ. ያ ትንሽ ልጅ እንደ ልማዱ እየሮጠ መጣ፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሥነ ጽሁፍ

ማስታወሻ

ግጥም፡- አንድን ነገር ወይም ድርጊት አድምቆና አጉልቶ የማሳየት፣ ሃሳብን አክርሮና አግዝፎ የማቅረብ ሃይል ያለው በጥቂት ምርጥ ቃላት ብዙ ሃሳብን የሚያስተላልፍ ለስሜት ቅርብ የሆነ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው፡፡

የግጥም ሙያዊ ቃላት

1 ስንኝ፡- በግጥም ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ መስመር ስንኝ ይባላል፡፡

ምሳሌ፡- አይዞህ የኔ ጌታ ነገርህን አትርሳ፣(ስንኝ )1
አለስልሰህ ዝራ የስንዴውን ማሳ፡፡(ስንኝ)2

2.ሐረግ፡- የስንኝ ግማሽ ወይም በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ የስንኝ አካል ነው፡፡

ምሳሌ፡- እምቢልታ መለከት/ የሚሰማው የት ነው፣
(ሐረግ1) (ሐረግ 2)
አንዱም በስርቆሽ በር/ አንድም በግቢ ነው፡፡
(ሐረግ 1) (ሐረግ 2)

3.አንጓ፡- በግጥም ውስጥ አንድ ሃሳብ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የስንኞች ስብስብ ነው፡፡
4.ቤት፡-በግጥም ውስጥ በመጨረሻ ስንኝ ላይ የሚገኙ የግጥሙ ማሳረጊያ ሆሄያት ናቸው፡፡
5.ቤት መምቻ ቃል፡-በተመሳሳይ ሆሄ በሚጨርሱ ስንኞች ውስጥ የመጀመሪያ ስንኝ የመጨረሻው ቃል ነው፡፡
ምሳሌ፡- ሰፌድና ወንፊት እያለ በጃችን፣
ያልተነፋ ዱቄት ምነው መብላታችን፡፡‹‹በጃችን›› ቤት መምቻ ቃል ነው፡፡
6.ቤት መድፊያ ቃል፡- በተመሳሳይ ሆሄ በሚጨርሱ ስንኞች ውስጥ የመጨረሻው ስንኝ የመጨረሻው ቃል ነው፡፡
ምሳሌ፡- ያቺን ትንሽ ፍጥረት ንብን ተመልከቱ፣
አታሳልፈውም ጊዜዋን በከንቱ፡፡‹‹በከንቱ››ቤት መድፊያ ቃል ነው፡፡
7.ቤት መታ፡- ግጥሙ በተመሳሳይ ሆሄያት ወይም ድምጾች ሲሰነኝ ነው፡፡
ምሳሌ፡- ከሰማይ ደመና ከላይ ተለይታ፣
ወደታች የመጣች የዝናብ ጠብታ፡፡
ሁለቱ ስንኞች በተመሳሳይ ሆሄያት ስለ ጨረሱ ግጥሙ ቤት መታ

በዚህ ግጥም ረቂቅ የሆነው ‹‹ጊዜ›› ተጨባጭ በሆነው ‹‹ባቡር›› ጋር አነፃፅሮ አቅርቧል፡፡
2.ምናባዊነት፡- ገጣሚ ጉዳዩ ያለውን ነገር ተመልክቶ በጥልቅ ስሜትና አገላለጽ ቀልብ እንዲይዝ አድርጎ ያቀርባል፡፡ በአይነ ህሊና የዳሰሰውን ነገር ምስል ከሳች በሆኑ ቃላት አማካኝነት አንባቢው ያ ስሜት እንዲሰማው ያደርጋል፡፡ ከሁሉም የስነ-ፅሁፍ ዘርፎች ምናባዊነት በግጥም ውስጥ ጎልቶ ይታያል፡፡
3.ቁጥብነትና እምቅነት፡- ግጥም በትንሽ ቃላት ብዙ ሃሳብ የሚያስተላልፍ ነው፡፡ ቁጥብ ማለት ብዙ አለማለት ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚመነጨው ከእምቅነት ነው፡፡ ግጥም እንደ ፈንጂ ፈንድተው ብዙ ሃሳብ በሚያስተላልፉ በጥቂት ቃላትና ሐረጋት ይዋቀራል፡፡ በአጠቃላይ ግጥም በትንሽ ቃላት ብዙ ሃሳብ የሚተላላፍበት የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው፡፡
ምሳሌ፡- እልፍ ከሲታዎች ቀጥነው የሞገጉ፣

ስጋችን የት ሄደ ብለው ሲፈልጉ፣
በየሸንተረሩ በየጥጋጥጉ፡፡
አስሰው አስሰው በምድር በሰማይ፣
አገኙት ቦርጭ ሆኖ ባንድ ሰው ገላ ላይ፡፡

(ምንጭ፡- በእውቀቱ ስዩም፣የግጥም ስብስቦች፣2001፣ገፅ 17)

4.ሙዚቃዊነት፡- የግጥም ሙዚቃዊነት የሚቀናጅበት የራሱ ስልት አለው፡፡
በተወሰነ የጊዜ ሁኔታ በሚደጋገሙ ድምፆች ሙዚቃዊነት ይገኛል፡፡ እነዚህ ደግሞ ምት ይባላሉ፡፡የግጥም ሙዚቃዊነት ጎልቶ የሚታየው ሲነበብ ነው፡፡
(ምንጭ፡- ኑሩ ኢብራሂም፣ ኤክስትሪም፣አማርኛ አጋዥ መፅሃፍ፣2012፣ገፅ 112-113፡፡)

ማስታወሻ

ጅምር ስንኞችን ማሟላት

ጅምር ስንኞችን የማሟላት ስራ ሲሰራ የሚተኮርባቸው ጉዳዮች አሉ። ከነዚህም አንዱ የሃሳብ ቁርኝት ነው። ለምሳሌ ግጥሙ ባለ ሁለት ስንኝ ግጥም ቢሆን ሁለቱ ስንኞች የሃሳብ ተያያዥነት ሊኖራቸው ይገባል። አንደኛው ስንኝ ስለ አንድ ጉዳይ፣ሌላኛው ስንኝ ደግሞ ስለ ሌላ ጉዳይ ሊያተኩሩ አይገባም። ምጣኔውም፣ሌላ ሊተኮርበት የሚገባ ነጥብ ነው። የመጀመሪያው ስንኝ የሀረጉና የስንኙ መጠን፣ ከሁለተኛው ስንኝ የሀረግና የስንኝ መጠን ጋር የተመጣጠነ መሆን ይኖርበታል። ሌላው የቤት ጉዳይ ነው። የመጀመሪያው ስንኝና የሁለተኛው ስንኝ የመጨረሻ ሆሄ ወይም ድምፅ ተመሳሳይነት ሊኖራቸው ይገባል።

ተግባር

1.ቀጥለው የቀረቡትን ጅምር ግጥሞች አሟሉ።

ሀ. ውሃ ጠማኝ ስላት ጠላ እየሰጠችን፣
…………………… ጉድ አደረገችኝ።

ለ.እጃችንን ታጥበን ምግብ ከበላን፣

ሁሌም ጤናችንን……………….።

ሐ. ከተማ ተስፋፋ መንገድም ተሰራ፣

ዘመኑም የልማት…………………።

መ. አንኳን መፃፍ ማንበብ ፊደል ሳያጠና፣

…………………….ይመስለዋልና።

ሠ. የበራውም ጠፍቶ…………….፣

የቆመውም ወድቆ የሳቀ ያለቅሳል፡፡

2.ከዚህ በታች ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቁ ስንኞችን የያዙ ግጥሞች ቀርበዋል፡፡ በተመሳሳይ ሆሄ የሚጨርሱትን ስንኞች በአንድ ላይ አምጥታችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. እንኮዬ ደማሜ ያለመጠን ፈርታ
ሳታስበው ድንገት ፍሙን ጨበጠችው
አያጅቦ ሲጮህ ትናንትና ማታ
እሳት ዳር ነበረ የተቀመጠችው

ለ. አላገኙም ነበር የሚያስታርቅ ሰው
አሁን ግን ሁለቱ መሃንዲስ መርጠው
እሳትና ውሃ ሲጣሉ ኖረው
ለአለም ሊያበሩ ነው እሳት ልጅ ወልደው

ሐ. ጉልበት እንዲሰጠኝ አምላኬን ለመንኩት
ትልቅ ሰው እሆን ዘንድ ነበረ ምኞቴ
ህፃንነት ለቆኝ ስሆን እንደወጣት
በጮርቃነት ዘመን በህፃንነቴ

መ. ማን ሊኖር እንደ ሆድ መብቱን ያስጠበቀ
አካላትን ማርኮ እሚውል ከጎጆ
ሲጎድል እያንኳኳ ግብር የጠየቀ
አሻፈረኝ ቢሉት ጦርነት አውጆ

## የክለሳ ጥያቄዎች

1.‹‹ነገርሻት››በሚለው ግስ ውስጥ ባለቤት አመልካች ቅጥያው የትኛው ነው?

ሀ. -ነገር. -ኣት ሐ. -ት መ.-ሻት

2.ከሚከተሉት አያያዥ ቃላት መካከል ተቃራኒ ሃሳቦችን የያዙ ሁለት አረፍተ ነገሮችን ሊያያይዙ የሚችሉ የትኞቹ ናቸው?

ሀ.በመሆኑም ለ.ቢሆንም

ሐ. ስለዚህ መ. በዚህም

3.ገንዘብ የሰጡኝ እነሱ ናቸው፡፡ በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል መደብና ቁጥር ምንድን ነው?

ሀ.ሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር

ለ.አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር

ሐ. ሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር

መ.ሦስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር

4.ግጥም ከዝርው ጽሁፍ የሚለይባቸውን ባህርያት ጥቀሱ፡፡

5.የግጥም ሙያዊ ቃላትን ጥቀሱና ለእያንዳንዳቸው ማብራሪያ ስጡ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## አርበኝነት

የምዕራፉ ዋና ዋና ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ካዳመጣችሁት ምንባብ ለወጡ ጥያቄዎች ምክንያታዊ ምላሾች ትሰጣላችሁ፡፡
- ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ አረፍተ ነገሮችን ታሟላላችሁ፡፡
- የተመለከታችሁትን ሁነት መሰረት በማድረግ ትናገራላችሁ፡፡
- የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም አንብባችሁ ትረዳላችሁ፡፡
- የንባብ ስልቶችን ትጠቀማላችሁ፡፡
- የምንባቡን ታሪክ አሳጥራችሁ ትፅፋላችሁ፡፡
- ለቃላት ተቃራኒ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ለቃላት ቀጥተኛ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- የስም አይነቶችን ከአረፍተ ነገር ውስጥ ትለያላችሁ፡፡
- ምሳሌያዊ ንግግርን በአውድ ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡-ማዳመጥ
### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1.ሜትሮሎጂ ምንድነው?

2.የአየር ንብረት ለውጥ ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ምን ማለት ነው?

### ተግባር

1.መምህራችሁ ‹‹የአየር ንብረት ለውጥ›› በሚል ርዕስየሚያነቡላችሁን ምንባብ አዳምጣችሁ ከዚህ በታች የቀረቡትን ባዶ ቦታዎች አሟሉ፡፡

ሀ.የአየር ንብረት የሚባሉትየዳመና፣የንፋስ፣-----------------የቅዝቃዜ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

ለ.የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤው የህዝብ ቁጥር መጨመር፣----------እና የጸሃይ ብርሃን መለዋወጥ ነው፡፡

2.ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት››ትክክል ካልሆነ ደግሞ ‹‹ሐሰት››በማለት መልሱ፡፡ ያላችሁበትንም ምክንያት አብራሩ፡፡

ሀ.የአየር ንብረት ለውጥ ሙሉ በሙሉ ሰው ሰራሽ ነው፡፡

ለ. ለአየር ንብረት ለውጥ የሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡

ሐ. ኢንዱስትሪዎች ሲጨምሩ የሐይል ፍጆታ ይቀንሳል፡፡

መ.ከተለያዩ ፋብሪካዎች በካይ ጋዞች መለቀቅ ለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ ነው፡፡

ሠ.የእሳተ ገሞራ ፍንዳታና የፀሐይ ብርሃን መጠን መለዋወጥ ሰው ሰራሽ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር

ከዚህ በታች የቀረበውን ሁነት መሰረት በማድረግ የተለያዩ መረጃዎችን በማንሳት ተነጋገሩበት፡፡

ሀ. በዚህ ዘመን በሀገራችን በተለይም በመዲናችን አዲስ አበባ የመኪና አደጋ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል፡፡ በእናንተ እይታ ይህ አደጋ መንስኤው የእግረኞች ነው? ወይስ የአሽከርካሪዎች? ከእግረኛም ይሁን ከአሽከርካሪስ ምን ይጠበቃል? ተወያዩበት፡፡

ለ. ከትምህርት ቤታችሁ ወይም በተለያዩ ከብዙሃን መገናኛዎች የሚተላለፈውን የትራፊክ መመሪያዎች ምን ያህል እየተገበራችሁት ነው? የየራሳችሁን ተሞክሮ ለክፍል ጎደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡



## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1.የአርበኛ የህይወት ታሪክን መፃፍ ለምን ያስፈልጋል?

2. አርበኝነት ሲባል ምን ይመስላችኋል?

3. የአንድ ግለሰብ የህይወት ታሪክ ሲፃፍ ምን ምንን ያካትታል ብላችሁ ታስባላችሁ?

4. በታሪክ የምታውቋቸውን አርበኞች ጥቀሱ፡፡

## ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ

የኢትዮጵያ ጀግኖች ታሪክ ሲነሳ፣ በግንባር ቀደም ከሚጠቀሱት መካከል ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ አንዱ ናቸው ይጠቀሳሉ፡፡ ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ በኦሮሚያ ክልል ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ወሊሶ በሚባለው ቦታ በነሐሴ ወር መጨረሻ በ1854 ዓ.ም ተወለዱ፡፡ እኚህ ታላቅ ጀግና ገና በልጅነት እድሜያቸው በጦር ሜዳ ውስጥ የተገኙ ሰው ነበሩ፡፡ በጎልማሳነታቸውም ወቅት የመድፍ ተኩስ ተምረው ከፈረንሳይ ሀገር የተሰጣቸውን መድፍ የሚተኩስና የሚያስተኩስ ጀግና ወጣቸው፡፡ በመድፍ አስተኳሽነት በሰሩት ጀግንነትም ይታወሳሉ፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የተደረጉትን ጦርነቶችም መድፉን ወደ ጠላት ወረዳ ተኩሰው ጠላትን የሚያርበደብዱ ጀግና ሆኑ፡፡ በተለይም ኢትዮጵያ ከጣሊያን ጋር ባደረገችው የ1888 ዓ.ም ጦርነት ወቅት በመቀሌ፣ በአዲግራትና በአድዋ ተራሮች መድፋቸውን ጠምደው፤የጣሊያንን ጦር በርቀት በመምታት ዝናን ያተረፉ ጎበዝ ተሰኙ፡፡ በኢትዮጵያ በኩል የተተኮሰው የመድፍ ጥይት የጣሊያኑ መድፍ አፍ ውስጥ ገብቶ እሳትም ተነስቶ ሁለት ወታደሮችና አፈር የተሞሉ የምሽግ ጆንያዎች

ተቃጠሉ። እሳቸውም በማዕረግ ላይ ሌላ ማዕረግ ተጨምሮላቸው ደጃዝማች ተብሎ ስማቸው በወርቅ ቀለም ከተፃፈላቸው ጀግኖች መካከል አንዱ ሆኖ ተጠራ። ከጦርነትና ከጀግንነት ውጭ ሌላ ህይወት ለሌላቸው ለነደጃዝማች ባልቻ አይነቶች እንዲህ ተባለላቸው።

ጦር መጣ ጦር መጣ ጫፉን ነቀነቀው፣

ጎበዝን ደሰ አለው ፈሪንም ጨነቀው።

ጣሊያን ለሁለተኛ ጊዜ ኢትዮጵያን ሲወር ከዚያን ዘመን ጀግኖች መካከል የቀሩት ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ ብቻ ነበሩ። በወቅቱ አዲስአበባ ሙሉለሙሉ በጣሊያን አገዛዝ ስር ወድቃለች። አባ ነፍሶም አምስትሺህ ያህል ጦራቸውን ይዘው በአዲስ አበባ በደቡብ በኩል በእኩለ ቀን ገብተው የጣሊያንን ጦር ለመምታት ተዘጋጁ። ደጃዝማች ባልቻ ጦራቸውን አምጥተው አሁን ‹‹አየርጤና›› ከሚባለው ሰፈር ማዶ ካለው ረጂ ጋራ ላይ መሸጉ። ከዚያም መድፋቸውን ጠምደው የሌሎቹን አርበኞች ሁኔታና መልዕክት መጠባበቅ ጀመሩ። ሁኔታውን ለመሰለል ሌሊቱን ወደ አዲስ አበባ የላኳቸው ወታደሮቻቸው ጣሊያኖቹ ጋር ሳይደርሱ በባንዳዎች ተይዘው ተገደሉባቸው። ሲነጋ ጣሊያን በአውሮፕላን ሆኖ የደጃች ባልቻን ጦር እየተከተለ በጣም ብዙ ሰው ፈጀባቸው። በህይወት ዘመናቸው ጣሊያንን ሁለት ጊዜ የተዋጉትና ብዙ ሺህ ተከታይ የነበራቸው ባልቻ አባ ነፍሶ ብቻቸውን ቀሩ። በመጨረሻ ጥቂት ወታደሮቻቸውን ይዘው ወደ ኋላ አፈገፈጉ።



**ጊዜ ንባብ ጥያቄ፡-ባልቻ አባ ነፍሶ ጦራቸውን ይዘው አዲስ አበባ በደቡብ በኩል የገቡት ለምን ያመስላችኋል?**

የደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ ታሪክ በጣሊያኖች ዘንድ ሲወራ ብዙዎችን አስገረመ፡፡ ‹‹ በአድዋ ጦርነት ከተዋጉት ሰዎች መካከል ባልቻ አባ ነፍሶ የሚባል የ75 ዓመት ሽማግሌ ሰው አሁን በህይወት አለ፡ ፡ በደቡብ በኩል ጦር እያደራጀ ነው›› ተብሎ እየተጋነነ ሲወራ የጣልያን መንግስት ‹‹ይህን ሰው እንፋረደዋለን ከነ ህይወቱ ይዛችሁ እንድታመጡት፡፡›› የሚል ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ ‹‹....የጠላት ጦር ደጃዝማች ባልቻ ወደሚኖሩበት እስከ ጉራጌ ሀገር ድረስ በመዝለቅ በሰዎች ላይ ዘመተባቸው፡፡ ህዝቡም ከዳቸው፤ ወታደሮቻቸውም ለህይወታቸው ሲሉ ሸሹ፡፡ ደጃዝማች ባልቻና ሁለት አሽከሮቻቸው ከሳቸው ጋር ሶስት ሰዎች ብቻ ቀሩ፡፡ ያ ሁሉ የጣሊያን ጦር ከበባቸው፡፡ ወዴትም መሄድ አልቻሉም፡፡

በመጨረሻም አንድ ነጭ ፈረንጅ ወደ ደጃች ባልቻ ዘንድ መጣ፡፡ ከዚያም....‹‹ደጃዝማች ባልቻ ማለት አንተ ነህ?›› አላቸው፡፡

ደጃዝማቹም ‹‹አዎ እኔ ነኝ!›› ሲሉ፤ ፈረንጁ ‹‹በሉ ይማረኩ፤ ሽጉጥዎትንም ያስረክቡ፡፡›› አላቸው፡፡ ደጃዝማች ባልቻም፤‹‹ እኔ እጅ የምሰጥ ሰው አይደለሁም፡፡ ትጥቄንም አልሰጥህም!›› ብለው ሽጉጣቸውን አውጥተው፤ ነጩን የጣሊያን ጦር መኮንን ገደሉት፡፡

እንግዲህ የደጃዝማች ባልቻ የጀግንነት ታሪክ በተለይ ከአድዋ ድል በኋላ እየገነነ መጥቶ የመድፈኛ ክፍል ሃላፊ ከመሆን ጀምሮ፣ የጦር ግምጃ ቤት ሲቋቋም፤ የግምጃቤቱ ሃላፊ ሆነው ዛሬ ከበቅሎ ቤት በታች ይገኝ ከነበረው ስፍራ ላይ የኢትዮጵያን ጦር መሳሪያ በአይነት በአይነት ማስቀመጥ መጀመራቸው ይታወቃል፡፡ ስለ ስራቸውም ክብር ታላላቅ ቦታዎች በስማቸው ተሰይመዋል፡፡ ከነዚህም መካከል በሩሲያውያን እርዳታ የተገነባው ደጃዝማች ባልቻ ሆስፒታል፣ ደጃዝማች ባልቻ መንገድ፣ ደጃዝማች ባልቻ ትምህርት ቤት ከብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እኚህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ለሃገራቸው ህዝብ ያደረጉት ታላቅ ጀብዱ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ ይኖራል፡፡

(ምንጭ:-ዳግማዊ ነቃጥበብ፣አዲስ 1879 ያልተዘመረላቸው፣ከሚለው መፅሐፍ ለመማርያነት እንዲያመች ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡

## ተግባር

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. የደጃዝማች ባልቻ የጀግንነት ታሪክ እየገነነ የመጣው መቼ ነው?
2. ደጃዝማች ባልቻ ከጦርነትና ከጀግንነት ውጭ ሌላ ሕይወት የላቸውም ሲባል ምን ማለት ነው?
3. የደጃዝማች ባልቻ የትውልድ ቦታ የት ነው?
4. ደጃዝማች ባልቻ ወደ አዲስ አበባ የገቡት ምን ያህል ጦራቸውን ይዘው ነው?

5. የደጃዝማች ባልቻ ወታደሮች ለምን ሸሹ?
6. ጦር መጣ ጦር መጣ ጫፉን ነቀነቀው፣
ጎበዝን ደስ አለው ፈሪንም ጨነቀው። የሚለው የቃል ግጥም የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድነው?
7. ደጃዝማች ባልቻ ወደ አዲስ አበባ የላኳቸው ወታደሮች የተገደሉት በማነው?
8. ደጃዝማች ባልቻ ጣሊያንን የተዋጉት ለስንተኛ ጊዜ ነው? ማብራሪያ ስጡ።

2.ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት››ትክክል ካልሆኑ ደግሞ‹‹ሐሰት›› በማለት መልሱ።

1.ጦር እያደራጀ ነው ተብሎ እየተጋነነ የተወራለት የጣሊያኑ መኮንን ነው።

2. ለደጃዝማች ባልቻ ክብር በስማቸው ከተሰየሙት ቦታዎች መካከል ደጃዝማች ባልቻ ትምህርት ቤት ይጠቀሳል።

3. የመጀመሪያው የጣሊያን ጦርነት የተካሄደው በ1888 ዓ.ም ነው።

4. ደጃዝማቹን ከነህይወቱ ይዛችሁ እንድታመጡት የሚል ትዕዛዝ ያስተላለፈው የጣሊያኑ መንግስት ነው።

5. ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ በመጨረሻ ትጥቃቸውን ለነጩ ጣሊያን ሰጥተዋል።

3. በ ‹‹ሀ›› ስር ለተዘረዘሩት ቃላት ምንባቡን መሰረት በማድረግ በ‹‹ለ›› ከተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳያቸውን አዛምዱ።

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1.አስገረመ | ሀ. የሚያስፈራሩ |
| 2. እየገነነ | ለ. ጠላቶች |
| 3. ተሰኙ | ሐ. ከፍ እያለ |
| 4 የሚያርበደብዱ | መ. ሸሹ |

5. ባንዳዎች ሠ. አስደነቀ

6. አፈገፈገ ረ. ተባሉ

ማስታወሻ

## የንባብ አይነቶች

ንባብ ከተለያዩ ምንጮች መረጃን ለመሰብሰብ ያገለግላል፡፡ ንባብ ሙሉ ሰው ያደርጋል፡፡ አንድ ሰው ንባብ በሚያነብበት ጊዜ የምንባቡ ግብ መሆን ያለበት የምናነበውን ፅሁፍ መረዳት ነው፡፡ እንደምናነብበት ዓላማና የአነባበባችን አይነት ንባብን ለአራት እንከፍለዋለን፡፡ እነሱም፡-

ሀ.የዝግታ ንባብ፡- ይህ የንባብ አይነት አንድን ጉዳይ በጥልቀት በመመርመር፣ በመተንተንና በመገምገም የምናነብበት ነው፡፡ ይህ የንባብ አይነት የምርምር ጽሁፎችንና በተለይ ለፈተና በምንዘጋጅበት ጊዜ የምንጠቀመው ነው፡፡

ለ.ሰፊ ንባብ፡- ይህ የንባብ አይነት እንደ ልቦለድ ያሉ አዝናኝና ሰፋፊ ጽሁፎችን ጥልቀት ሰጥተን በፍጥነት ለማንበብ ይጠቅማል፡፡

ሐ. የአሰሳ ንባብ፡- ይህ የንባብ አይነት ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የምንፈልገውን አንኳር ሃሳብ በአፋጣኝ አንብቦ ለማግኘት ይጠቅማል፡፡ በዚህ የንባብ ስልት ስዕሎች ፣ግራፎች፣ ሰንጠረዦችና የግርጌ ማስታወሻዎች ከፍተኛ ጥቅም አላቸው፡፡

መ. የገረፍታ ንባብ፡- ይህ የንባብ አይነት በጽሁፍ ውስጥ ትኩረት የሚሰጠውን ዝርዝር መረጃ ሳይሆን አጠቃላይ የጽሁፍ ሃሳብ ለመጨበጥ የሚጠቅም ነው፡፡ በዚህ ስልት ምንባብ ስናነብ መስመር በመስመር እያሰስን ሳይሆን አጠቃላይ ሃሳቡን ብቻ መጨበጥ ነው፡፡

(ምንጭ፡- ኑሩ ኢብራሂም፣ ኤክስትሪም፣ አማርኛ አጋዥ መፅሀፍ (2012፣ ገፅ 199-200፡፡

## ክፍል ኣራት፡- መጻፍ

### ተግባር

1. በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን የደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ ታሪክ በድጋሚ አንብባችሁ ከዚህ በታች የቀረቡትን ቅደም ተከተሎች መሰረት በማድረግ ታሪካቸውን አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡

-የትውልድ ዘመን

- የትውልድ ቦታ

- ከማን ጋር ተፋለሙ?

- በጎልማሳነት እድሜ ምን አደረጉ?

- ያተረፉት ዝና ምንድነው?

-ነጩ ፈረንጅ ወደ ባልቻ የመጣው ምን ሰምቶ ነው?

## ክፍል አምስት፡-ቃላት

### ተግባር

1.ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺያቸውን ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ጣፋጭ | 6. ስውር |
| 2. ጭካኔ | 7.አደነቀ |
| 3. ተቃዋሚ | 8.ጎረምሳ |
| 4. ግርድፍ | 9.ጥንታዊ |
| 5. ባላንጣ | 10. ሀሩር |

2.ለሚከተሉት ቃላት ቀጥተኛ ፍች ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| 1.ጥረት | 6.አከተመ |
| 2.ጠርዝ | 7. አመነታ |
| 3.ጥሪት | 8.ተሰጥኦ |
| 4.አሜኬላ | 9.መንደር |
| 5. ተቋዳሽ | 10.ስሌት |

## ክፍል ስድሰት:- ሰዋሰው

ማስታወሻ

የስም ዓይነቶች፡-

በአማርኛ ቋንቋ የስም አይነቶች በአምስት ክፍል መመደብ ይቻላል፡፡ እነዚህም፡-

1. የተፀውኦ ስም፡- አንድ ነገር ብቻውን ተነጥሎ የሚታወቅበት የግል መጠሪያ ስም ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. የሰዎች ስም፡- ናኦል፣ ጂቱ

ለ የተራራ ስም፡- ቱሉ ዲምቱ፣ ባቱ

ሐ. የወንዞች ስም፡- አባይ፣አዋሽ

መ. የሀይቆች ስም፡- ጣና፣ላንጋኖ

ሠ. የቦታዎች ስም፡- ነቀምቴ፣ ጂማ

ረ. የሀገር ስም፡- ኢትዮጵያ፣ ቻይና

ሰ. የክስተት ስም፡- ጸሀይ፣ ጨረቃ

2. የወል ስም፡- የተወሰኑ ነገሮች በጋራ የሚታወቁበት ወይም የሚጠሩበት መጠሪያ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሰው፣ መኪና፣ ቤት፣ወንድ፣ወታደር

3. የጥቅል ስም፡- የተለያዩየወል ስም ያላቸው ነገሮች ተጠቅለው በደፈናው የሚታወቁበት መጠሪያ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ህዝብ፣እህል፣ አትክልት፣ እንስሳ

4. የቁሳቁስ መጠሪያ ስም፡-ለማንኛውም የመገልገያ እቃ በመጠሪያነት የሚያገለግል የስም ዓይነት ነው፡፡ ምሳሌ፡- አልጋ፣ወንበር፣ድስት

5.የረቂቅ ነገሮች መጠሪያ ስም፡- ይህ መጠሪያ ስም በዓይን የማይታዩና በእጅ የማይዳሰሱ ረቂቅ ነገሮች የሚጠሩበት ነው፡፡

ምሳሌ፡- መንፈስ፣ ነፍስ፣ ፍቅር

(ምንጭ፡ ኑሩ ኢብራሂም፣ ኤክስትሪም፣ አማርኛ አጋዥ መፅሀፍ (2012፣ ገፅ 37-39፡፡

## ተግባር

በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት በየትኛው የስም ዓይነት እንደሚመደቡ ለዩ፡፡

ምሳሌ፡ሰበታ ለአዲስ አበባ ቅርብ የሆነች ከተማ ናት፡፡
ሰበታ የሚለው ስም የቦታ ስም ነው፡፡

1.በክረምት ወቅት የአዋሽ ወንዝ ሞልቶ ይፈሳል፡፡
2. አዳማ ውብ ከተማ ናት፡፡
3. ራሄል ጥሩ ስነ ምግባር አላት፡፡
4. ከአፍሪካ ውስጥ በከፍታ አንደኛው ተራራ ኪሊማንጃሮ ነው፡፡
5. ብሩክ ጥሩ ውጤት ስላመጣ ከፍተኛ ደስታ ተሰማው፡፡

## ክፍል ስድስት፡-ሥነ-ጽሁፍ

ማስታወሻ

ሥነ-ቃል፥ በመነገር፣በመተረት፣በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩልዩ ክስተቶችንና የህይወት መልኮችን መግለጫ ኪነ ጥበብ ነው፡፡

የስነ-ቃል አይነቶች ብዙ ናቸው፡፡ በየአገሩና በየባህሉ የተለያዩ የስነ

ቃል አይነቶች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ በሁለት አበይት ቅርፆች ይከሰታሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ በዝርውና በትረካ የሚነገሩ ሲሆን፣ ሁለተኛዎቹ በግጥም ቅርፅ የሚቀርቡና የሚዜሙ ናቸው፡፡

1. በዝርው ከሚቀርቡት መሃል፡- ተረት፣ አፈታሪክ፣ሀተታ ተፈጥሮ፣ ምሳሌያዊ አነጋገር፣ እንቆቅልሽ፣ ቀልድ ሌሎችም … ይገኙበታል፡፡

ከተዘረዘሩት መካከል ምሳሌያዊ ንግግርን እንመልከት፡-

ምሳሌያዊ ንግግሮች፡- በማህረሰቡ ዘንድ ጠቃሚና ተፈላጊ መግባቢያዎች ናቸው፡፡ ሰዎች ብሶታቸውን፣ ሃዘናቸውን፣ አመለካከታቸውን ያንፀባርቁባቸዋል፤ እምነታቸውን ይገልፁባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ቅሬታቸውን ያሳውቁባቸዋል፤አስነዋሪ ተግባራቸውን ይነቅፉባቸዋል፡፡ ጎጂ ድርጊቶችን ያወግዙባቸዋል፤ ሰናዮዎቹንም ያወድሱባቸዋል፡፡

2. በግጥም ቅርፅ የሚቀርቡ፡- ባህላዊ ዘፈኖችና ዝማሬዎች፣ ሙሾን፣ ፉከራንና ቀረርቶን መጥቀስ ይቻላል፡፡

(ምንጭ፡-ዘሪሁን አስፋው፣የስነ-ጽሁፍ መሰረታውያን፣(2007)፣ገፅ 20 እና 29፡፡

## ተግባር

1.የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች በቀረበው ምሳሌ መሰረት የሚነገሩበትን አውድ ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ.‹‹ስም ከመቃብር በላይ ይውላል፡፡›› ሰናይ ልማድን የሚገልፅ ነው፡ ማለትም መልካም ስራ የሰሩ ሰዎች ቢሞቱም በስራቸው ምክንያት ሲታወሱ ይኖራሉ ማለት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ለ. ‹‹ሰነፍ ይዘራል እንጂ አያርምም፡-›› ስንፍናን የሚያወግዝ ነው፡

የጀመረውን ስራ የማይጨርስ ማለት ነው፡፡

1. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር፡፡
2. አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል፡፡
3. ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም፡፡
4. በሽታውን የደበቀ መድሐኒት አይገኝለትም፡፡
5. ፈሪ የሚያባርረው ሰው ሳይኖር ይሸሻል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በዝርው ከሚቀርቡ የስነ ቃል አይነቶች አይመደብም፡፡

ሀ.ተረት ለ.ምሳሌያዊ አነጋገር ሐ.ፉከራ መ.እንቆቅልሽ

2.የተወሰኑ ነገሮች በጋራ የሚጠሩበት መጠሪያ ስሞች-------ይባላሉ፡፡

ሀ.የወል ስም ለ. የጥቅል ስም ሐ. የቁሳቁስ ስም

መ.የረቂቅ ነገሮች መጠሪያ ስም

3.የሚከተሉትን ቃላት በስም አይነታቸው መድቡ፡፡

1. ኬኒያ
2. ሳራ
3. ዳሽን
4. ፍራፍሬ
5. ጠረጴዛ

4.አራቱን የንባብ ዓይነቶች የእያንዳንዳቸውን ምንነት አብራሩ፡፡

5.የሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚያስተላልፉትን መልዕክት ግለጹ፡፡

ሀ. በጨው ደንደስ፣ በርበሬ ተወደስ፡፡

ለ.ዝም ባለ አፍ ፣ዝንብ አይገባበትም፡፡

ሐ.እህልን አላምጦ፣ ነገርን አዳምጦ

# ምዕራፍ ስድስት

## ልቦለድ

የምዕራፉ ዋና ዋና ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ በቃል ትመልሳላችሁ፡
- በሰፊ የቡድን ውይይት ላይ ትናገራላችሁ፡፡
- በምንባቡ መሰረት ለቃላት ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡
- አዳዲስ ቃላትን ለመረዳት ቁልፍ ቃላትን አንብባችሁ ትገነዘባላችሁ፡፡
- ስለ ስደት ሁኔታ የተረዳችሁትን ትፅፋላችሁ፡፡
- የአጭርና የረጅም ልቦለድን ልዩነት ትፅፋላችሁ፡፡
- ውስብስብ አረፍተ ነገርን ትፅፋላችሁ፡፡
- ውስብስብ ቃላትን ትለያላችሁ፡፡
- የስም ገላጮችን( ቅፅሎችን) ከአረፍተ ነገር ውስጥ ትለያላችሁ፡
- ግስና ተውሳከ ግስን ከአረፍተ ነገር ውስጥ ትለያላችሁ፡፡
- የአጭር ልቦለድን ጭብጥ ትናገራላችሁ፡፡

### ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. አካል ጉዳተኝነት ማለት ምን ማለት ነው ?እንዴትስ ይከሰታል ?
2. ስለ አካል ጉዳተኝነት ያላችሁን አስተሳሰብ ግለፁ?

### ተግባር

1 መምህራችሁ ‹‹አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ›› በሚል ርዕስ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

ሀ. ብዙ አካል ጉዳተኞች የትምህርት እድል የማያገኙት ለምንድነው?
ለ. የአካል ጉዳተኞች የመማር መብት በምን በምን መደገፍ አለበት ትላላችሁ?
ሐ. አካል ጉዳተኞች ያሉባቸው ችግሮች ምን ምን ናቸው?
መ. የሴት አካል ጉዳተኞች ችግር ‹‹ድርብርብ›› ነው ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

2. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆኑትን ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆኑትን‹‹ሐሰት›› በማለት መልስ ስጡ፡፡

1 . ትምህርት ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቹ ናቸው፡፡

2. አካልጉ ዳተኞችን ማገዝና መንከባከብ የቤተሰብ ሃላፊነት ብቻ ነው፡፡

3. በአለም አቀፍ ደረጃ አምስት ቢሊዮን የሚሆኑ ሰዎች አካል ጉዳተኞች ናቸው፡፡

4. አካል ጉዳተኞች የመማርና የመስራት እድሉን ካገኙ የአቅም ውስንነት የለባቸውም፡፡

5. ለአካል ጉዳተኞች የመረጃና የቴክኖሎጂ ተደራሽነት ከፍተኛ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት መናገር

### ተግባር

1.የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው መልሱ፡፡

ሀ.በሬዲዮ ከሚተላለፉ ትረካዎች ውስጥ ያዳመጣችሁትን ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

ለ.ከዚህ በፊት ያነበባችሁት አጭር ልቦለድ ካለ ከማህበረሰቡ አኗኗር ጋር ያለውን ግንኙነት ተነጋገሩበት፡፡

ሐ.የምታውቁትን ተረት ወይም ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሶስት፡-ማንበብ

### ልቦለድ

ልቦለድ በእውኑ አለም በሰዎች የህይወት ገጠመኝ ከተፈጸመውና ሊፈጸም ከሚችለው በከያኒው ግንዛቤና አመለካከት ተቀምሮ የሚቀርብ የማህበረሰቡ ቁሳዊና ህሊናዊ ገፅታ የሚታይበት ኪነታዊ ስራ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ በአንድ ልቦለድ ውስጥ ደራሲው የሚያቀርበውም በተወሰነ ቦታ፣ በተወሰነ ታሪካዊ ዘመን በሚኖር ማህበረሰብ ውስጥ ሊከሰቱ ይችላሉ ወይም ተከስተዋል ብሎ የሚያምንባቸውን የተለያዩ ህይወታዊ ክንዋኔዎችንና ሰብአዊ እውነታዎችን እንዲሁም የሰዎችን ባህሪያት ነው፡፡ ደራሲው እንዲህ በሚያደርግበት ጊዜ ግን የዘመኑን ባህል፣ የዘመኑን ማህበረሰባዊ እውነታ በውል ያሳየናል፡፡

ልቦለድ ማህበራዊ ህይወትን በስፋት በሚጥምና በሚስብ ዘይቤ የማሳየት አቅም ያለው፤የሰውን ልጅ አያሌ ገጠመኞች ማቅረብ የሚችል ኪነ ጥበባዊ ቅርጽ ነው፡፡ ከሌሎቹ የስነ ጽሁፍ ዘርፎች

የበለጠ ዘላቂነት ያላቸው የተስፋፉና የበለጸጉ የሰው ምስሎችን የመያዝ አቅም አለው፡፡ በልቦለድ የሰው ልጅ ሀዘንና ደስታ፣ ጥላቻና ፍቅር፣ ምኞትና ፍላጎት፣ ብልጽግናና ውድቀት፣ባጠቃላይ ግብሩና አተያዩ በኪነታዊ ዘዴ ይቀርባል፡፡

የለቦለድ ዓይነቶች ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም፡- ረጅም ልቦለድና አጭር ልቦለድ ናቸው፡፡

1. ረጅም ልቦለድ፡-ይህ የልቦለድ ዓይነት የገጸባህርያትን ሰፊ የህይወት ገጠመኝ የሚዳስስ፣ ሰፊ የመቼት ገለጻ ያለው፣ ብዙ ጭብጦችን የሚያነሳ፣ ከአንድ በላይ ታሪክ የሚያቀርብ፣ ከአንድ በላይ ጭብጥ የሚይዝና ባጠቃላይ ነገሮችን ከችኮላና ከጥድፊያ ይልቅ በስፋትና በዝርዝር የሚያቀርብ የልቦለድ ዓይነት ነው፡፡ ረጅም ልቦለድና አጭር ልቦለድ በፈጠራ ጽሁፍነታቸው ተመሳሳይነት ሲኖራቸው በመጠን ግን ልዩነት ይኖራቸዋል፡፡ ረጅም በመሆኑም በሚቀርበው ታሪክ ውስጥ በርካታ ገጸ ባህርያትን ማሳተፍ ከመቻሉም በላይ የነዚህን ገጸ ባህርያት ህይወት ከልደት እስከ ሞት በስፋትና በጥልቀት ለማሳየት በቂ ቦታና ጊዜ አለው፡፡

2. አጭር ልቦለድ፡-አጭር ልቦለድ በተወሰነ መቼት፣ ገጸባህርይና ድርጊቶች አማካኝነት ወደ ነጠላ ውጤት የሚጣደፍ ስለያንዳንዱ ነገር ሰፊ ገለጻ የማይሰጥ የልቦለድ ዓይነት ነው፡፡ አጭር ልቦለድ አንድን ጉዳይ ብቻ መርጦ በትኩረት የሚያይና ብዙ ሳይጠማዘዝ ቶሎ ቶሎ ወደፊት የሚገሰግስ ነው፡፡

## የአጭር ልቦለድ ባሕርያት

አጭር ልቦለድ ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች የሚለይበት ሶስት ባህርያት አሉት፡፡ እነሱም፡- ጥድፊያ፣ ቁጥብነትና ነጠላ ውጤት ናቸው፡፡

1.ጥድፊያ፡- የሚተረከው ታሪክ ብዙ ሳይጠማዘዝ ቶሎ ቶሎ መተረክ አለበት፡፡ ትልሙና የተለያዩ ክፍሎቹ ፍሰታቸውን ጠብቀው ዝርዝር

ነገር ሳያበዙ፤ የተስፋፉ የመቼት ገለጻና የገጸባህርይ ዳራ ሳይሰጡ በፍጥነት መንዝ አለባቸው፡፡

2.ቁጥብነት፡-የአጭር ልቦለድ አላባውያን አንዱ ከአንዱ ጋር የተሳሰሩ ሆነው ቅንጅት ይፈጥራሉ፡፡ አንድ አላባ ከሌላው ጋር በመቆራኘት ዝርዝር ነገሮችን ከማንሳት ተቆጥቦ ባጭሩ ነገሮችን ሲያቀርብ ነው፡፡

3.ነጠላ ውጤት፡-ሁሉም የአጭር ልቦለድ አካላት ተሳስረው ወደ አንድ ዋነኛ ትኩረት የሚፈሱበትና ደራሲው በአንባቢው አእምሮ ተቀርጾ እንዲቀር የሚፈልገው አንድ ኪነጥበብ ነው፡፡

(ምንጭ፣ዘሪሁን አስፋው፣ የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን፣2007)

ተግባር

1. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት››ትክክል ካልሆነ ደግሞ‹‹ሐሰት›› በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. ልቦለድ ማህበራዊ ህይወትን በስፋት፣ በሚጥምና በሚስብ ዘይቤ የማሳየት አቅም አለው፡፡
2. ረጅም ልቦለድ በባህርይው መጠነ ሰፊ ነው፡፡
3. ረጅም ልቦለድ ከአንድ በላይ ታሪክ የሚያቀርብ ነው፡፡
4. አጭር ልቦለድ የረጅም ልቦለድ አንድ ምዕራፍ ነው፡፡
5. አጭር ልቦለድ መቼቱ ሰፊ ነው፡፡
6. አጭር ልቦለድ የገፀ-ባህሪያትን ታሪክ ከልደት እስከ ሞት ይተርካል፡፡

2. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በተጠየቃችሁት መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጡ፡፡

1.ረጅም ልቦለድ ከአጭር ልቦለድ የሚለይበት------ነው፡

ሀ.ሰፊ መቼት መግለፁ ለ.ብዙ ጭብጦች ማንሳቱ

ሐ.ከአንድ በላይ ታሪክ ማቅረቡ መ.ሁሉም መልስ ናቸው ፡፡

2.በልቦለድ የሰው ልጅ----------እና-------በኪነታዊ ዘዴ ይቀርባል፡፡

ሀ.ሀዘንና ደስታ ለ.ጥላቻና ፍቅር ሐ.ብልፅግናና ውድቀት መ.ሁሉም

3.የረጅም ልቦለድ ባህርይ ያልሆነው?

ሀ. በርካታ ገፀ ባህሪያት ማካተቱ ሐ.ተቆጥቦ ነገሮችን ማንሳቱ

ለ. የፈጠራ ስራ መሆኑ መ.ብዙ ጭብጦችን ማንሳቱ

4.ከሌሎች የስነፅሁፍ ዘርፎች የበለጠ ዘላቂነት ያላቸው የተስፋፉና የበለፀጉ የሰው ምስሎችን የመያዝ አቅም ያለው------ነው፡፡

ሀ. ሥነ ቃል ለ. ልቦለድ ሐ. ግጥም መ.ግለታሪክ

5.የአጭር ልቦለድ ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. መቼት ለ. ጥድፊያ ሐ.ነጠላ ውጤት መ.ቁጥብነት

2.ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥ የሚኖራቸውን አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

ምሳሌ፡-መቆራኘት፡- መያያዝ

1. ሳይጠማዘዝ፡-
2. ዳራ፡-
3. ተሳስረው፡-
4. ጭብጥ፡-
5. ዘላቂነት፡-
6. ተቀምሮ፡-

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### ተግባር

1.የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው መልሱ፡፡

ሀ.ስለ ስደት አሰከፊ ገጽታ የምታውቁትንና ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የምታገኙትን መረጃ መሰረት በማድረግ ከ 50ቃላት ባልበለጠ አንድ አንቀፅ ፃፉ፡፡

ለ..የአጭርና የረጅም ልቦለድን አንድነትና ልዩነትን ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ተግባር

1.የሚከተሉትን ቃላት ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሃላፊነታችንን፡- ሃላፊ-ነት-ኣችን-ን

ቤታችን፡- ቤት-ኣችን

1.ጥንታዊነት፡-

2. ክፍሎቹ፡-

3. ተማሪዎቻቸውን፡-

4. ፍላጎታቸውን፡-

5.ወንድሞችሽ፡-

6.መግለጫዎች፡-

7.እንደገፈፈው፡-

8.አስፈተለችው፡-

2. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍች ስጡ፡፡

ምሳሌ፡-1. ምርቃት፡- እርግማን

2. ሲሻር፡-
3. ሰበሰበ፡-
4. ጥፋት፡-
5. ቀዥቃዣ፡-
6. የግል፡-
7. ጉዳት፡-
8. አሉታዊ፡-
9.ያፋጥናል፡-
10.ደግ፡-

## ክፍል ስድስት፡-ሰዋስው

1.የሚከተሉትን ነጠላ አረፍተ ነገሮች በማገናኘት ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ደበላ ነገ ፈተና አለበት፡፡

ለማጥናት ወደ ቤተ መፅሃፍት ሄደ፡፡

ደበላ ነገ ፈተና ስላለበት ለማጥናት ወደ ቤተ መፅሃፍት ሄደ፡፡

1. እራቱን ቶሎ በላ፡፡
   ጥናቱን ጀመረ፡፡
2. ቅዝቃዜ ተሰማው፡፡
   ህፃኑ አለቀሰ፡፡
3. ቁርሷን በላች፡፡
   ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡
4. መምህሩ መጡ፡፡
   ተማሪዎች ከወንበራቸው ተነሱ፡፡
5. ያኔት በጣም ራባት፡፡
   ያኔት አምርራ አለቀሰች፡፡

2. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የስም ገላጮችን(ቅፅሎችን) ለይታችሁ አውጡ፡፡

ምሳሌ፡- ትሁት ሰው በብዙዎች ዘንድ ይመሰገናል፡፡ ትሁት የስም ገላጭ( ቅፅል) ነው፡፡

1. ጠፍጣፋ ድንጋይ ለመቀመጫ አዘጋጀሁ፡፡
2. ደግ ሴት የተቸገረ ሰው ትረዳለች፡፡
3. ወፍራሙ ነጋዴ ሱቁ ውስጥ ተቀምጧል፡፡
4. ሱዳናዊ አርሶ አደር ተዋወቅኩ፡፡
5. አያሌ ሰዎች ተሰበሰቡ፡፡

3. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ግስና ተውሳከ ግስን ለይታችሁ አውጡ፡፡

ምሳሌ፡- ልጁ ምንኛ ያሳዝናል፡፡ ‹‹ምንኛ›› ተውሳከ ግስ ሲሆን ያሳዝናል የሚለው ደግሞ ግስ ነው፡፡

1. የትምህርት እድሉ ቶሎ መጣለት፡፡
2. ሲንጊተን ዘንድሮ ይመረቃል፡፡
3. ሴና ትኬት ለመቁረጥ በሌሊት ተሰለፈች፡፡
4. ረድኤት ክፉኛ አለቀሰች፡፡
5. ጎበዙ ተማሪ ዘወትር ያጠናል፡፡፡- ስነ-ጽሁፍ

## ክፍል ሰባት

## አንድ ፉርኖ

‹‹ስለእመብርሀን …ስለ ጭንቅ አማላጇ…›› እንዲህ እንዳሉ ስድስት ሰዓት ሆነ፡፡ በበራፋቸው እንደ ሌላው ቀን የሚመላለስ አልነበረም፡፡ አምስት ሳንቲም ሳያገኙ ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡ የሚበሉት አልጠፋም፡፡ ከትናንት ወዲያና ትናንት የተገኘ ምግብ አለ፡፡ ሳንቲም ቤሳ ቤስቲን የላቸውም፡፡ ምሳቸውን በልተው ደግመው በራፋቸው ላይ ወጡ፡፡ ‹‹ስለእመብርሀን…››አስር ሰዓት ሆነ፡፡

ሆዳቸውን ገልጠው ማከክ ጀመሩ፡፡ አድጎ በተቆለመመ ጥፍራቸው ያከኩት ሆዳቸው ሊጥ የፈሰሰበት አስፋልት መሰለ፡፡

ትንሽ ሰዓት ቀርቷቸዋል፡፡ ‹‹ፉርኖ ዳቦ›› ለመግዛት የሚያስችላቸውን ሳንቲም ለማግኘት ግን አልቻሉም፡፡ የትም ሄደው ጠግበው ቢበሉ ማምሻው ላይ አንድ ፉርኖ ዳቦ ገዝተው ካልበሉ ሆዳቸው ባዶ የሆነ ይመስላቸዋል፡፡ ረሀብ ይጠናባቸዋል፡፡

አስር ሳንቲም አስር ሰዓት ላይ አገኙ፡፡ አስር ሳንቲም ቀርቷቸዋል፡፡ ለወትሮው በዚህ ሰዓት ብዙ ፍራንክ ያገኛሉ፡፡ መንደርተኛው ይወዳቸዋል፤በተለይ ወጣቶቹ፡፡ አመሻሽ ሲጀምር ነው ቀስ እያሉ ወደ ዳቦ መሸጫው የሚሄዱት፡፡ ዳቦ ሻጮቹ ለምደዋቸዋል፡፡ ‹‹አንድ ፉርኖ መጡ፡፡›› ይሏቸዋል፡፡
አሮጊቷ የለመዱት ሰዓት ሲያልፍባቸው ሆዳቸውን ይሞረሙራቸው ጀመር፡፡ ትናንትን ናፈቁ፡፡ አንዳች የሚያህል ዳቦ ባምስት ሳንቲም፣ ከጥቂት አመታት በፊት ባስር ሳንቲም በልተዋል፡፡ ያኔ የምትጣፍጠዋን ትንሽዬ ፉርኖ ባቅራቢያቸው ከሚገኘው ኬክ ቤት ባምስት ሳንቲም እየጣፈጣቸው በልተዋል፡፡ ዘመኑ ደግ፡፡

‹‹ስለእመብረሀን…›› አስራሁለት ሰዓት ሆነባቸው፡፡ እንደ ህጻንልጅ ሆዳቸው ሲጮህ ተሰማቸው፡፡ አስር ሳንቲሟን በደቀቁ እጆቻቸው እየተቀባበሉ ተጫወቱበት፡፡ ለዓይን መያዝ ሲጀምር ከተቀመጡበት ተነሱ፡፡ የዳቦ ቤቱን ወጣቶች ‹‹ነገ አስር ሳንቲም አመጣለሁ፡፡›› ብለው ሊወስዱ፡፡ ሁለት እርምጃ እንደተራመዱ አንድ ትልቅ ሰው አምስት ሳንቲም ሰጥቷቸው አለፉ፡፡

‹‹እውር አሞራ የምትቀልብ እያለህ ጾሜን አላድር›› አሉ ድምጽ አውጥተው በቤታቸው ምንም የሚቀመስ እንደሌለ ሁሉ፡፡
ዳቦ ቤቱ በር ላይ ሊደርሱ ሲሉ አንዲት ሴት አምስት ሳንቲም ሰጠቻቸው፡፡ ‹‹የእለት እንጀራዬን የማትነሳኝ ተመስገን›› አሉና በረቁ፡፡ በጨርቅ ተደግፋ የታሰረች መነጽራቸውን ከፍ ከፍ እያደረጉ እንደ መጨፈር ቃጣቸው፡፡ ፉርኖ ባስር ሳንቲም ዱቤ አለማምጣታቸው አስደሰታቸው፡፡

ወደ ውስጥ ሲዘልቁ ከሳቸው በስተቀር ማንም ገዢ አልነበረም፡፡ ‹‹ አንድ ፉርኖ መጡ አለች ቀይዋ ዳቦ ነጋዴ ‹‹ኮሜስታሬ›› አሏቸው በባዶ ድዳቸው ፈገግ እያሉ፡፡

‹‹ቤኔ ቤኔ›› አሏቸው እየሳቁ ጣልያን ቤት እሰራ ነበር ይላሉ፡፡ አሮጊቷም ሆኑ ልጆቹ ‹‹ቤኔ ቤኔም›› ‹‹ከሜስታሬም››ምን ማለት እንደሆነ አያውቁም፡፡ እሳቸውም፤ እነሱም ይላሉ፡፡

አሮጊቷ ወደ ባንኮኒው ጠጋ አሉና ድፍን አስር ሳንቲምና ሁለት አምስት ሳንቲሞች በኩራት አስቀምጠው ‹‹ቶሎ በይ መሽቷል አንድ ፉርኖ›› አሉ፡፡

‹‹አንድ ፉርኖ እኮ ሰላሳ ሳንቲም ሆኗል›› አለቻቸው፡፡ ‹‹ምነው … ምነው ማታ በሀያ ሳንቲም በልቼ፡፡›› አሉ ሆዳቸው ይበልጡኑ ጮኸ፡፡ ሀያ ሳንቲም ለማግኘት አስራ ሁለት ሰዓት ተቀምጠዋል፡፡ ‹‹አይ እማማ በትናንት በሬ ማን ያረሰ አለ? ትናንትማ ትናንት አለቀ፡፡ ጠዋት ነው ሰላሳ የሆነው እንዳልሞላሎት ምንም የለኝም›› አለች ቀይዋ ዳቦ ሻጭ፣ የመሞቻቸው ቀን እንደተነገራቸው ሁሉ ደነገጡ፡፡

‹‹ክፉ ቀን ድንገት ይመጣል›› አሉ በሆዳቸው፡፡ በሀያ ሳንቲም ትኩስ ፉርኖ የበሉባት ትናንት ይበልጥ ናፈቀቻቸው፡፡ ረሀባቸው ጸና፡፡ ‹‹እሺ ነገ አመጣለው፣ በጥዋት›› አሉ አንድ ፉርኖ፡፡ ‹‹ስለ ነገ ማን ያውቃል?›› አለች ልጅቱ፡፡ ‹‹ግድ የለም አልሞት፡፡ እድሜዬም ረጅም የሆነው ፉርኖ ሲጨምር ለመሳቀቅ አይደል? …›› የሞጨሞጩ አይኖቻቸውን አሹ የዳቦ ሱስ ያናወዛቸው ምስኪን…ደፉን ቀስ እያሉ እየወጡ፡፡

(ምንጭ ጽጌሬዳ ሀይሉ፣ ፍለጋ፣ 2001፣ 1-2)፡፡

### ተግባር

1.ከላይ የቀረበላችሁን አጭር ልቦለድ መሰረት በማድረግ ተከታዮቹን ባዶ ቦታዎች አሟሉ፡፡

ሀ. ዋና ገፀ-ባህርይ

-----------------------------

ለ. ንዑሳን ገፀ-ባህሪያት

-----------------------------------

------------------------------------

------------------------------------

ሐ. ጭብጥ

----------------------------------------

----------------------------------------

---------------------------------------

2.ለሚከተሉት ጥያቄዎች በልቦለዱ መሰረት በቃል መልስ ስጡ፡፡

1.አሮጊቷ ‹‹እውር አሞራ የምትቀልብ እያለህ ጾሜን አላድር›› ያሉት ለምንድነው?

2. ዳቦ ሻጯ ‹‹በትናንት በሬ ማን ያረሰ አለ?›› ያለችው ለምንድነው?

3. የአሮጊቷ ቅፅል ስም ማነው?

4. አሮጊቷን የበለጠ የሚወዷቸው እነ ማን ናቸው?

5. አሮጊቷ ‹‹የዕለት እንጀራዬን የማትነሳኝ ተመስገን›› ብለው የቦረቁት ለምንድነው?

## የክለሳ ጥያቄዎች

1.ጎረቤታችን ራሱን እስኪስት ድረስ ገና በጠዋቱ ለምን እንደሚጠጣ ይገርመኛል፡፡ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ከየትኛው የቃል ክፍል ይመደባል?

ሀ. ቅፅል ለ.ተውሳከ ግስ ሐ. ግስ መ. ስም

2.ጎበዝ የሆኑ ሰዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች የመወጣት ብቃት አላቸው፡፡ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የስም ገላጩ … ነው፡፡

ሀ. ጎበዝ የሆኑ ሰዎች ለ .ጎበዝ ሐ. ችግሮች
መ. የመወጣት ብቃት

3.ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. እየተደረገልኝ
ለ. እንዳስጀመሩት
ሐ የአካባቢያችንን
መ. እየተጠቀሙበት
ሠ. ከጠቀሜታቸው

4. የአጭር ልቦለድን ባህርያት ዘርዝሩና የእያንዳንዳቸውን ምንነት አብራሩ፡፡

5. ዋና ገፀ-ባህርይ ማለት ምን ማለት ነው? አብራሩ፡፡

6.ንዑስ ገፀ-ባህርይ ማለት ምን ማለት ነው? አብራሩ፡

# ምዕራፍ ሰባት

## ሱስ

የምዕራፉ ዋና ዋና ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ ስለምታይዋቸው ሱሶች ትናገራላችሁ፡፡
- ክርክር ታደርጋላችሁ፡፡
- ከመስክ ጉብኝት ያገኛችሁትን ሃሳብ ትናገራላችሁ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡
- የድርሰት አይነቶችን ትለያላችሁ፡፡
- ድርሰት ትፅፋላችሁ፡፡
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- የግስ አይነቶችን ትለያላችሁ፡

ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1.ቀጥሎ የቀረበውን ስዕል ተመልክታችሁ ከስዕሉ የተረዳችሁትን ተናገሩ፡፡



## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ተግባር

1.መምህራችሁ ‹‹የታክሲ ላይ ጥቅስ›› በሚል ርዕስ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ፡፡

1.ከኳስ ሜዳ የሚመለሱ ተሳፋሪዎችን የጫነችው ታክሲ ምን የሚል ማሳሰቢያ ነው የለጠፈችው?

ሀ. ሲጋራ ማጨስ ክልክል ነው፡፡

ለ.የማጨስ አመል ያለበት መሳፈር አይችልም፡፡

ሐ.የትም ቦታ ሲጋራ ማጨስ ክልክል ነው፡፡

መ.ሲጋራ ማጨስ የተፈቀደ ነው፡፡

2.በታክሲው ውስጥ ቀድሞ ሲጋራ የለኮሰው ማነው?

ሀ. ተሳፋሪ ለ.ሹፌሩ ሐ. ረዳቱ መ.ሁሉም ተሳፋሪ

3.ተሳፋሪዎቹ እርስ በእርስ የተያዩት ለምንድነው?

ሀ. ተሳፋሪው ሲጋራ ለኩስልኝ ማለቱ ገርሟቸው፡፡

ለ. የሹፌሩ ሲጋራ ማጨስ ገርሟቸው፡፡

ሐ. ጽሁፉን ተመልክተሃል የሚለው የሹፌሩ ንግግር ገርሟቸው፡፡

መ.ሲጋራ ማጨስ ክልክል ነው የሚለው ገርሟቸው፡፡

4. በታክሲው ውስጥ የተለጠፈው ፅሁፍ ባለቤት ማነው?

ሀ. የታክሲው ነጂ ሐ. ተሳፋሪዎች

ለ. የታክሲው ባለንብረት መ. ታክሲዋ

5. ሹፌሩ እየነዳት ያለው ታክሲ የማን ነች ?

ሀ. የራሱ የሹፌሩ ለ. የጓደኛው ሐ.የዘመዱ

መ.የተሳፋሪዎቹ

6. የአዲስ ከተማ ልጆች የሲጋራ አጫሾችን ፍቅር ይስጥህ የሚባባሉት……ነው።

ሀ. አጫሾች ስለማይጨካከኑ

ለ.ሱሰኞች አለመጨካከናቸውን ለማሳየት

ሐ.ከመዋደዳቸው የተነሳ ሁሉም ጉዳይ ላይ መጠቃቀማቸው

መ. ሀእና ለ መልስ ናቸው

2. ባዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ተሳፋሪው እና ሹፌሩ የተነጋገሩበት አውድ ትህትና የተላበሰ ነው? ወይስ አይደለም? ምሳሌ በመስጠት አብራሩ።

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከአካባቢያችሁ በመጠየቅ መልስ ስጡ።

ሀ. በታክሲ ውስጥ የሚፃፉ የተለያዩ መልዕክት ያላቸውን ጥቅሶች በመሰብሰብ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ለ. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ፓርኮች በጉብኝት የተመለከታችሁትን ወይም ያገኛችሁትን አዲስ ነገር ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ማስታወሻ

## የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ

ክርክር በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተቃራኒ እይታ ባላቸው ሁለት ሰዎች (ቡድኖች) መካከል ተናግሮ ለማሳመን የሚካሄድ ሙግት ነው፡፡ ሙግቱ የተሟጋቾችን ሃሳብ መዝነው ፍርድ የሚሰጡ ዳኞች ይኖሩታል፡፡ ተከራካሪ ወገኖችም በቂ ዝግጅት ማድረግና የክርክር አቀራረብ ስልትን ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

1.የክርክር ዝግጅት፡-

- ርዕሱን በሚመለከት ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ሃሳብ መሰብሰብ፡፡

-ከሰበሰባችሁት ሐሳብ ውስጥ ለክርክሩ ጠቃሚ ናቸው የምትሏቸውን መምረጥ፡፡

-የሚቀርቡበትን ቅደም ተከተል መወሰን፡፡

-የመከራከሪያ ሃሳባቸውን ከማቅረባቸው በፊት ልምምድ ማድረግ፡፡

-በክርከሩ ላይ ሥነ ስርዓት ጠብቃችሁ መገኘት፡፡

2. የክርክር አቀራረብ

-ደግፋችሁ ወይም ተቃውማችሁ የምትከራከሩበትን ርዕስ ማስተዋወቅ፡፡

- የመከራከሪያ ሃሳባችሁን በቅደም ተከተል በቃል ማቅረብ፡፡

- ሃሳባችሁን በተገቢ የአካል እንቅስቃሴ ማገዝ፡፡ - ተቃዋሚያችሁ

የሚያነሳቸውን ነጥቦች በትክክል መመዝገብና የተቃውሞ ሃሳብ ማዘጋጀት፡፡

- ለክርክሩ በሚሰጣችሁ ጊዜ በሚገባ መጠቀም፡፡

- ከርዕሳችሁ ላለመውጣት መጠንቀቅ፡፡

- ሃሳባችሁን ምስጋና በማቅረብ ማጠናቀቅ፡፡

3. ከላይ የቀረበውን መመሪያ በመከተል ‹‹ሱስን ማቆም ይቻላል ወይስ አይቻልም?›› በሚል ርዕስ ላይ ቡድን መስርታችሁ ተከራከሩ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

## ሱስ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ሱስ በአንድ ግለሰብ፣ በቤተሰብ እንዲሁም በሃገር ላይ ያለው ተፅዕኖ ምንድነው?
2. ወጣቶች በተለያዩ ሱሶች ውስጥ እንዲጠመዱ የሚያደርጓቸው ምክንያቶች ምን ምን ይመስላችኋል?
3. ጫት በመቃም የሚባክነውን ጊዜ ለስራ ብንጠቀምበት ምን ጥቅም የምናገኝ ይመስላችኋል?

## ሱሰኝነትና መዘዙ

ሱሰኝነት ማለት በተለያዩ ሱስ አምጭ ነገሮች በመጠመድ ሰውነት ሱስ የተያዝንበትን ነገር ካላገኘ መስራት የሚገባውን ነገር መስራት ያለመቻል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው በሲጋራ ሱስ የተያዘ ከሆነ ሲጋራውን አግኝቶ ካላጨሰ ደስታ ይርቀዋል፤ ምንም አይነት ተግባር ለመፈጸም ፍቃደኛ አይሆንም፡፡

ሱስ አንዴ ከተለመዱ በኋላ በየጊዜው ውል የሚል አምሮት ወይም ልማድ ነው። ሱስ አምጭ የሚባሉ ነገሮች በአይነታቸው በርካታ ናቸው። ከነዚህ መካከል፡- ሲጋራ ማጨስ፣ ጫት መቃም፣አደንዛዥ ዕጽ መውሰድና የአልኮል መጠጦችን መጠጣት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።
እነዚህ ነገሮች አንዴ ከተለመዱ በቀላሉ መተው አስቸጋሪ የሚሆኑና በየጊዜው እንድንወስዳቸው ግድ የሚሉን ስር የሰደዱ ልማዶች ናቸው። አንድ ሰው ሱስ ከሚያሲይዙ ነገሮች በአንዱ ተጠምዶ ያን የተጠመደበትን ነገር መተው ካልቻለና ለመተው ፍቃደኛ ካልሆነ በተጨማሪም ሱስ የተያዘበትን ነገር ካላገኘ የዕለት ተግባሩን ማከናወን እስከማይችልበት ደረጃ ከደረሰ ሱሰኛ ነው ማለት ይቻላል። በሱስ ለመያዝ እንደ ምክንያት የሚወሰዱት እነዚህ ሱስ የሚያመጡ ነገሮች በሚወሰዱበት ጊዜ በአእምሮ ላይ የ ሚፈጥሩት ጊዜያዊ የደስታ፣ዕርካታና የመነቃቃት ስሜቶች እንደሆኑ ምርምሮች ያረጋግጣሉ። አእምሮም ከነዚሁ ሱስ አምጭ ነገሮች ጋር ከተላመደ ያለማቋረጥና በብዛት እንድንወስድ ያስገድደናል። በዚህም ሳቢያ አእምሯችን ለሱስ ተገዢ ይሆናል።
ሲጋራ ማጨስና ጫት መቃም ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትሉ ናቸው። ሲጋራ ማጨስና ጫት መቃም የስራ ፍቅርና ታታሪነትን ያሳጣሉ። ሰርተን የምናገኘውን ገንዘብ ለቁም ነገር እንዳናውለው ያደርጋሉ። ከሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት እንዳይኖረን ያደርጋሉ ጤንነታችንን በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳሉ። በየለቱና በብዛት በተወሰዱ መጠን የውስጥ አካልን ጉዳት ላይ ይጥላሉ። ለምሳሌ፡-፤ለሳንባቲቢ፣ለጉበት፣ለልብ፣ ለደም ግፊትና ለተለያዩ የካንሰር አይነቶች
ለአእምሮና ለነርቭ ህመም ያጋልጣሉ። ስለዚህ ‹‹ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ›› እንደሚባለው ከዚህ የችግር ባህር ውስጥ ገብተን ራስን፣ ቤተሰብንና ሀገርን ጉዳት ላይ እንዳንጥል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል።

(ምንጭ፡- ከቀድሞው ሰባተኛ ክፍል ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ተግባር

1.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል መልስ ስጡ፡፡


1. ሱሰኝነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ሱሰኞች ከገቡበት ሱስ ለመውጣት እየፈለጉ መውጣት የማይችሉት ለምን ይመስላችኋል?
3. በምንባቡ የተጠቀሱት የሱስ አይነቶች ምንምን ናቸው? ምንስ ጉዳት ያስከትላሉ?
4. አንድ ሰው ሱሰኛ ሆነ ማለት ምን ማለት ነው?
5. ‹‹ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ›› ሲባል ምን ማለት ተፈልጎ ነው?

2.ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ሱስን ማቆም ፈታኝ ነው፡፡ ፈታኝ የሚለው ቃል አውዳዊ ፍችው ‹‹አስቸጋሪ›› ማለት ነው፡፡

1. ሱስ የስራ ፍቅርን ያሳጣል፡፡
2. ሲጋራ ማጨስ ከሰውጋር ያለን መልካም ግንኙነትን ያጠፋል፡፡
3. የአልኮል መጠጦች ስር የሰደዱ ልማዶች ናቸው፡፡
4. በሲጋራ ሱስ የተያዘ ሲጋራውን አግኝቶ ካላጨሰ ደስታ ይርቀዋል፡፡
5. በሱስ የተያዘ ሰው ለተለያዩ በሽታዎች የመጋለጥ እድሉ ሰፊ ነው፡፡

3.ቀጥሎ የቀረበውን የቢጋር ሰንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ፡፡ ከዚያም ከምንባቡ ውስጥ ያገኛችሁትን መረጃዎች በሳጥኖቹ ውስጥ ሙሉ፡፡



## ክፍል አራት፡- መጻፍ

ማስታወሻ

### የድርሰት አይነቶች

ስለ ድርሰት አይነቶች የመስኩ ምሁራን የተለያዩ ሃሳቦችን ያስቀምጣሉ፡፡ አብዛኞቹ የድርሰት ዓይነቶችን በአራት በመክፈል ይስማማሉ፡፡ አራቱ የድርሰት ዓይነቶች፡-

1.ተራኪ ድርሰት 2.ገላጭ ድርሰት 3.ስእላዊ ድርሰት 4.አመዛዛኝ ድርሰት ናቸው፡፡

1.ተራኪ ድርሰት፡- አስቀድሞ ስለተከወኑ ጉዳዮች እንዲህ ሆነ ከዚያ እንዲህ ተደረገ በማለት በቅደም ተከተል ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ድረስ የሚያወጋ፣የሚተርክ ነው፡፡

ምሳሌ፡- አስር ዓመት ቢሆነኝ ነው፤ ያኔ ብሩኬ የአርት ት/ቤት ተማሪ ነበር፡፡ የትልቁ ቤት በረንዳ ላይ የስዕል እቃውን ደርድሮ የጦር አዋጊ ይመስል አሻግሮ ይመለከታል፡፡ እግሩን ከፊት አድርጎ እጆቹን ደረቱ ላይ አጣምሮ ከወጨጫ ተራራ ጋር የሃሳብ ሙግት ይገጥማል፡፡ አይኖቹን አጥብቦ ስንጥር የመሰለውን ሽንተረር ሳይቀር ሲያጠና ይቆያል፤ ሲጨርስ የተወጠረው ሸራ ፊት ለፊት አግዳሚ ወንበሯን እንደ ፈረስ ተፈናጦ ይቀመጣል፡፡ የተራራውን ያህል ባዶ ሸራ ላይ አፍጥጦ ብዙ ይቆያል፡፡ ከዚያ ድንገት ሸራ ላይ ያረፈች ዝንብ ይገድል ይመስል በፍጥነት ብሩሹን አውጥቶ ቀለሙን ነክሮ ቅጥ የሌለው መስመር ከወዲያ ወዲህ ያወናጭፋል…

2.ገላጭ ድርሰት፡-ገላጭ ድርሰት አስረጂ ድርሰት እየተባለ ይጠራል፡፡ ገላጭ ድርሰት የአንድን ነገር ምንነት፣ ባህርያት፣ቅርጽ፣ አይነት፣መጠን፣ አገኛኘት፣ አሰራር፣ ጠቀሜታ ወይም ጉዳት …

ለማብራራት የሚጻፍ ነው፡፡

ምሳሌ፡- አስም ምንድነው? ምንም አይነት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሳያሳይ የትንፋሽ እጥረት ወይም መታፈን ሲያጋጥም ሰዎች አስም ተነሳባቸው እንላለን፡፡ በትንፋሽ መታፈን ምክንያት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በየዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ይለያሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የአስም ጅማሮ ከእያንዳንዱ ሳል ጋር በተያያዘ ደረቅ ጉንፋን ይከሰታል፡፡

3.ስዕላዊ ድርሰት፡- ይህ የድርሰት ዓይነት ጸሃፊው በቃላት አማካይነት በአንባቢው አእምሮ ውስጥ ስዕል ለመከሰት የሚሞክርበት ነው፡፡ ‹‹ስዕላዊ ድርሰት የአንድን ነገር ሁናቴ በአይን እንዳዩት፣ በእጅ እንደዳሰሱት፣ በጆሮ በቅርብ ሆነው እንደሰሙት አድርጎ በጠቅላላው ግዙፍ አድርጎ የሚያቀርብ የድርሰት ዓይነት ነው፡፡››

(አምሳሉና ደምሴ፣ 1982፣130፡፡)

ምሳሌ፡- አጭር ሆኖ ጥርሳም ነው፤ ፀጉሩ ተመልጧል፤ መልኩም ጥቁር ነው፤ አፍንጫው ደፍጣጣ ከመሆኑ የተነሳ ሁለት ትንንሽ አይኖቹ የሚተያዩ ይመስላሉ፡፡ ከተፈጠረ ጫማ አድርጎ አያውቅም የሚለብሰው ቁምጣ ሱሪና በላብ የጠቆረ ሹራብ ነው፡፡ እውነተኛ ስሙ አይታወቅም፡፡ ሆኖም የሰፈሩ ጌሾ ወቃጭና ጥርሱ ገጣጣ በመሆኑ የመንደሩ ነዋሪዎች ውቃው ጥርሶ ይሉታል፡፡ ውቃው ድብልብልና ቅርጸ ቢስ ብቻ ሳይሆን ጥቁርና መልከ ቢስ በመሆኑ የሰፈሩ ልጆች ማስፈራሪያ ነው፡፡

4.አመዛዛኝ ድርሰት ፡-ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን በማምጣት የሚያነሳቸውን ጉዳዮች፣ ነገሮች ልዩነትና አንድነት፣ጥቅምና ጉዳት፣ መልካምና መጥፎ ጎን በተለያየ አቅጣጫ

በመመርመር አንዱ ከአንዱ የሚሻልበትን ወይም የሚለይበትን ነገር እያወዳደረና እያነጻጸረ የሚያቀርብ የድርሰት ዓይነት ነው፡፡

በዚህ ድርሰት ጸሃፊው በሚያቀርባቸው ጉዳዮች፣ ነገሮች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ለማንሳት በቂና አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ አንባቢውን ለማሳመን መጣር ይጠበቅበታል፡፡

ምሳሌ፡- ተማሪዎች የተለያየ የአጠናን ዘዴዎችን ይከተላሉ፡፡ አንዳዶቹ ፀጥታ የሰፈነበት አካባቢ ለጥናት አመቺ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ አእምሮን ካሳመኑ ድምፅ ያለበት አካባቢም ማጥናት ችግር እንደ ማይፈጥር ይናገራሉ፡፡ ይልቁንም በጣም ፀጥ ባለ ቦታ ማጥናት የመጫጫንና የመሰልቸት ስሜት ስለሚፈጥር አሉታዊ ጎን አለው ብለው ይከራከራሉ፡፡

(ምንጭ፡- ማርታ እሸቱ፣ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሰረት የተዘጋጀ፣ አማርኛ ለ9ኛና ለ10ኛ ክፍል፣ 2006፣52-54፡፡)

### ተግባር

1. ከአራቱ የድርሰት አይነቶች አንዱን መርጣችሁ ሶስት አንቀፅ ያለው ድርሰት ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

1. ለሚከተሉት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች ስጡ፡፡

1. ውጥን
2. መነቅነቅ
3. ረቂቅ
6. ማጤን
7. ማጎልበት
8. መቀራመት

4. መንስኤ

5. ኮረብታ

9. ባዘነ

10. በለፀገ

2.ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት በተመሳሳይ ፍቻቸው አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ሀ. ተጠቂ

ለ. ማሰናከል

ሐ. ህገ ወጥ

መ. ፈነጠዘ

ሠ. ቁልቁል

ረ. ተሸፈነ

ሰ. አጣደፈኝ

ሸ. የከፋ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

ማስታወሻ

የግስ አይነቶች የድርጊትና የሁነት ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

1.የድርጊት ግስ

ድርጊት አንድ አካል በሌላ አካል ላይ የሚፈፅመውን ተግባር ያመለክታል፡፡ ይህም ማለት አንድ ነገር በራሱ ወይም በሌላ ነገር ላይ የሚፈፅመውን ድርጊት ወይም ተግባር የሚገልፅ የግስ አይነት

ነው። ምሳሌ፡- ለሊሳ በግ ገዛ። ይህ አረፍተ ነገር ለሊሳ በግ ላይ የመግዛት ድርጊት ወይም ተግባር መፈፀሙን ይገልፃል። ድርጊቱን የሚገልፀው ‹‹ገዛ›› የሚለው ቃል ነው። ለሊሳ ደግሞ በግ ገዢ ሲሆን ድርጊቱ መገዛት ነው

2.የሁነት ግስ

የአንድን ነገር መፈጠር፣ መከሰት ወይም ወደ ሌላ ነገር መለወጥ የሚገልፅ የግስ አይነት ነው።

ምሳሌ፡- ፍቅርተ ወፈረች።

በሊና አዘነ።

በሁለቱ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ‹‹አዘነ›› እና ‹‹ወፈረች›› የሚሉት ግሶች ድርጊትን አያመለክቱም። ፍቅርተም ሆነች በሊና የፈፀሙት ድርጊት የለም። እነሱ ራሳቸው የሆኑት ወይም በነሱ ላይ የደረሰ ነገር አለ።

(ምንጭ፡- ባየ ይማም፣ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፣2010፣66 እና 70

ተግባር

1.የሚከተሉትን ግሶች የድርጊትና ሁነት በማለት ለይታችሁ አመልክቱ።

ምሳሌ፡- ‹‹ሸጠ›› የድርጊት ግስ ነው።

‹‹ረዘመ›› የሁነት ግስ ነው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሆነ | መታ | ዘመረ | ተከዘ |
| ቀደደ | ጠለለ | | ዘረፈ |
| ጨለመ | መረጠ | | ነው |

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ግሶች የድርጊት ግሶች ወይም የሁነት ግሶች በማለት ለዩ፡፡

ሀ. ሂክማ ዶሮ ገዛች፡፡

ለ. ደበላ የተመረዘ ምግብ ስለተመገበ ታመመ፡፡

ሐ. ድመቱ የህፃኑን ወተት ጠጣ፡፡

መ ከወንድሙ ጋር ስለተጣላ አኮረፈ፡፡

ሠ. ነጋዴው ያመጣውን ጫማ ሸጠው፡፡

2. ገበሬ ዓይነት ዓይነት አለው፡፡ ምስጉን ገበሬ አለ፤ሰነፍ ገበሬም አለ፡፡ምስጉን ገበሬ ከሰነፉ የሚለየው በስራውና በታታሪነቱ ነው፡፡ ይህ የድርሰት ዓይነት ….ነው፡፡

ሀ. ተራኪ ለ. ስዕላዊ ሐ. አመዛዛኝ መ. ገላጭ

3. የቀንበጥ ማራባት ዘዴ ግድ ከመሬት ላይ እንዲሆን አያስፈልግም፡፡ አፈሩን በታኒካ ወይም በሳጥን አድርጎ ቢተክሉት ይሆናል፡፡ ገበሬዎች ይህንን ዘዴ ተመልክተው እያፈራረቁ፣እያሻሻሉ ፣እየሞከሩ የበለጠ ውጤት አግኝተዋል፡፡ ይህ የድርሰት ዓይነት …ነው፡፡

ሀ. ገላጭ ለ.አመዛዛኝ ሐ. ተራኪ መ. ስዕላዊ

4. ነጋዴዎች የሚጠቀሙት ‹‹ራሳቸውን›› ወይስ ‹‹ህብረተሰቡን›› የሚለው ርዕስ ከሚከተሉት ስርዓቶች ውስጥ በየትኛው ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ሀ. በክርክር ለ. በጭውውት ሐ. በውይይት መ. በቃለ ምልልስ

5. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

1.ተመክሮ
2.ሩህሩህ
3.ታጋሽ
4. ወሮበላ
5.ገሃድ

# ምዕራፍ ስምንት

## የግብር አሰባሰብ ምንነት እና ጠቀሜታ

የምዕራፉ ዋና ዋና ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ካደመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ለጠቋሚ ቃላትና ሃረጋት ምላሽ ትሰጣላችሁ፡፡
- በቡድን ተወያይታችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- መረጃን መሰረት በማድረግ አጭር ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- በምክንያትና ውጤት የተሳሰረ አንቀፅ ትፅፋላችሁ፡፡
- የሚነበብላችሁን ጽሁፍ አዳምጣችሁ አሳጣራችሁ ትፅፋላችሁ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ተውሳከ ግሳዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግን ትለያላችሁ፡፡
- ከጽሁፍ ውስጥ ምሳሌያዊ አነጋገርን ታወጣላችሁ፡፡
- የዘይቤ አይነቶችን ትለያላችሁ፡፡

### ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

#### ተግባር

1. መምህራችሁ ‹‹ጠንካራ የስራ ባህል›› በሚል ርዕስ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ ካዳመጣችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ጠንካራ የስራ ባህል ከምን ይመነጫል?

2. በተሰማሩበት የስራ መስክ ተግቶ መስራት ምንን ያመለክታል?

3 .ጠንካራ የስራ ባህል ምንን ያሻሽላል?

4. ገቢ ባደገ ቁጥር ምን ይሻሻላል?

5. የጤና፣ የትምህርት የፍጆታ ግብአቶችን በማሟላት ምን መፍጠር ይቻላል?

2. ከዚህ በታች የቀረቡ ቃላትና ሐረጋት እንደ መነሻ ሀሳብ ተደርገው ካዳመጣችሁት ምንባብ የተወሰዱ ናቸው። ቃላትና ሀረጎቹ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ግለፁ።

1. ደቦ
2. የስራ ባህል
3. በራስ መተማመን
4. ማህበረሰባዊ ግንኙነት
5. መልካም ስነምግባር

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር

1.የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዳጠያየቃቸው መልስ ስጡ።

ሀ. አርአያነት ያለው ማህበራዊ ግንኙነት ማለት ምን ማለት ነው? በመወያየት ተናገሩ።

ለ. የተቸገሩና የታመሙ ሰዎችን እንዴት መርዳት እንደሚቻል ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1.ግብር ማለት ምን ማለት ነው?

2. ለአንድ ሀገር እድገት ግብር መክፈል ምን ጥቅም አለው?

3. በሀገራችን ሁሉም ማህበረሰብ ግብር በመክፈል ግዴታውን ይወጣል ብላችሁ ታስባላችሁ?

## ክፍል ሶስት፡-ማንበብ

## የግብር አሰባሰብ ምንነት እና ጠቀሜታ

መንግስት የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ገቢ እንደሚያስፈልገው እሙን ነው፡፡ የማንኛውም መንግስት ገቢ ምንጭ ደግሞ ታክስና ታክስ ነክ ያልሆኑ የገቢ ምንጮች ናቸው፡፡ ግብር መክፈል የውዴታ ግዴታ ነው፡፡ግብር መክፈል ሃገራዊ ግዴታ ብቻ ሳይሆን ዜጎች ለሃገራቸው ሲሉ ከሚያገኙት ላይ የሚከፍሉት የውዴታ ተግባርም ነው፡፡ የየትኛውም ሃገር መንግስት ከፍተኛ ገቢውን የሚያገኘው ታክስ በመጣልና በመሰብሰብ ነው፡፡ ታክስ የሚሰበሰበው በመንግስት ብቻ ነው፡፡ ይህ ማለት በዘመናዊ ታክስ ስርዓት ከፌዴራል ወይም ከክልል መንግስት በስተቀር ማንኛውም ሰው ወይም አካል ታክስ የመሰብሰብ መብት የለውም ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ታክስ መወሰንም ሆነ የመሰብሰብ ስልጣን ያለው መንግስት ብቻ ነው፡፡ መንግስት ይህንን መብት የሚያገኘው ከታክስ ከፋዮች ጋር በሚያደርገው ስምምነት ሳይሆን መንግስት በመሆኑ ብቻ ነው፡፡ ታክስ በሁኔታዎች ላይ አይመሰረትም፡፡ ግብር ከፋዩ ከሚፈልገው የታክስ ጥቅም ከመንግስት ካላገኘሁ አልከፍልም የሚል ሁኔታ አይኖርም ማለት ነው፡፡ ይልቁንም የመንግስት አላማን እውን ለማድረግ የራሱን ድርሻ መወጣት አለበት፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ወይም ደርጅት ለመንግስት

ታክስ ለመክፈል የሚገደደው ለሚከፍለው ታክስ ተመጣጣኝ የሆነ አገልግሎት ከመንግስት ወዲያውኑ ወይም ዘግይቶም ስለሚያገኝ ብቻ ሳይሆን ታክስ መክፈል የማይገዳደሩት ግዴታ ስለሆነ ነው፡፡

በእኛ ሃገር ግብር የሚለው ቃል እጅግ የተለመደ ቢሆንም ግብርንና ታክስን በተለዋዋጭነት መጠቀም የተለመደ አነጋገር ሆኗል፡፡ ታክስ የሚለው ቃል የእንግሊዝኛ ቃል ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ግን በሃገራችንም ውስጥ ልክ እንደ ማንኛውም የአማርኛ ቃል አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ታክስ የሚለው ቃል ማንኛውንም ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ የሚያካትት ሲሆን ግብር የሚለው ግን እንደ ገቢ ግብር ያሉትን የሚሸፍን ነው፡፡ ታክስ የሚሰበሰበው ህጋዊ በሆነ መልኩ ነው መንግስት ታክስ ወይም ግብር የሚሰበስበው ህጋዊ በሆነ መንገድ በሚሰራ ስራ ላይ ሆኖ በግብር እና ታክስ መመሪያና ደንብ መሰረት ነው፡፡ መንግስት ህጋዊ ያልሆነ ስራ ላይ ታክስ አይሰበስብም፡ ፡ታክስ ለጋራ ጥቅም የሚውል ነው፡፡ መንግስት ሰብስቦ ለከፈለውም፣ ላልከፈለውም አገልግሎት ለመስጠት በተለያዩ ሁኔታዎች ወጪ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም የመንግስት ወጪ ለሁሉም ነው፡፡ ስለዚህ ታክስ ለጋራ ጥቅም የጋራ መዋጮ የሚከፈል ነው፡፡ ታክስ የሚከፈለው በግለሰብ ገቢና በግብር ከፋይ ስራ እንቅስቃሴ ላይ በመመርኮዝ ነው፡፡ ምንም እንኳን ታክስ በግዳጅ የሚሰበሰብ መዋጮ ቢሆንም ገቢው በታክስና ግብር አዋጅ ካልተካተተ በስተቀር ሁሉም ሰው ወይም ድርጅት ታክስ እንዲከፍሉ አይገደዱም፡፡

ለምሳሌ አንድ ያልተቀጠረ ሰው ከመቀጠር የሚገኝ ግብር መጠየቅ የለበትም፡፡ ታክስ የሚጣለው በሁሉም ግለሰብ ወይም ድርጅት ላይ ሆኖ ገቢያቸው ታክስ ለመክፈል የሚያበቃቸው ሁሉ ይከፍላሉ፡፡ ስለዚህ ታክስ ዘርና እምነትን ሳይለይ የሚጣል ክፍያ ነው፡፡

ትልቁና ወሳኝ የታክስ ዓላማ ገቢን ማሳደግ ነው፡፡ ስለዚህ ዘመናዊ

አስተዳደርና አሰራር ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ግብርን መክፈል ምጣኔ ሃብትን ለማረጋጋት፣የተፋጠነ ምጣኔ ሃብታዊ እድገትን ለማረጋገጥና የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ያስችላል።

(http://WWW.Mor.gov.et/ የገቢዎች ሚኒስቴር ድህረ ገፅ)

## ተግባር

1.ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. የማንኛውም መንግስት የገቢ ምንጭ ምንድነው?
2. ታክስ የመወሰንም ሆነ የመሰብሰብ ስልጣን ያለው ማነው?
3. ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ለመንግስት ታክስ ለመክፈል የሚገደደው ለምንድነው?
4. ታክስ የሚሰበሰበው ህጋዊ በሆነ መንገድ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?
5. የታክስ ወይም ግብር የመክፈል ዓላማ ምንድነው?
6. ዘመናዊ አስተዳደርና አሰራር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ምን ምን አሻሽሏል?

2. በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት››ትክክል ካልሆነ ደግሞ‹‹ሀሰት›› በማለት መልስ ስጡ።

1.ታክስ የሚሰበሰበው በመንግስት ብቻ ነው።

2.መንግስት ታክስ ሰብስቦ ለከፈለውም ላልከፈለውም አገልግሎት ይሰጣል።

3. አንድ ሰው በስራ ከመቀጠሩ በፊት ግብር ይከፍላል።

4. መንግስት የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ገቢ ግዴታ አይደለም።

5. አልፎ አልፎ ማንኛውም ሰው ታክስ የመሰብሰብ መብት አለው።

3. ከዚህ በታች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ቃላት ቀርበዋል፡፡ ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አገባብ መሰረት ፍቻቸውን ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ታክስ፡- ግብር

1.ምንጭ

2. በመመርኮዝ

3. መሰብሰብ

4. ተግባራት

5. ተመጣጣኝ

4. ለሚከተሉት ቃላት መዝገበ ቃላትን ተጠቅማችሁ ቀጥተኛ ፍቻቸውን ስጡ፡፡

1. መዋጮ
2. ዘመናዊ
3. ስርአት
4. መገዳደር
5. የተለመደ

ማስታወሻ

## ምክንያትና ውጤት

ለአንድ ድርጊት መፈጸም እንደ መንስኤ የሚቀመጥ ነገር ምክንያት ይባላል፡፡ ምክንያትን መሰረት አድርጎ አንድ መደምደሚያ ላይ የሚደረስበት ሂደት ውጤት ተብሎ ይጠራል፡፡ በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ምክንያትና ውጤት ትስስር ሊኖረው ይገባል፡፡ ውጤት ላይ የሚደረሰው ምክንያትን መሰረት አድርጎ መሆን አለበት፡፡

ምሳሌ፡-1. ልጁ በደንብ ስላጠና ጥሩ ውጤት አመጣ፡፡

ምክንያት= በደንብ ማጥናቱ

ውጤት = ጥሩ ውጤት ማምጣቱ

ምሳሌ፡-2.

….ቤተሰብ ሲፈርስ ልጆች ከእናት ወይም ከአባት ጋር እንዲኖሩ አልያም ልጆቹን እኩል እንዲከፋፈሉ ይደረጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ወላጆች በጊዜያዊ መደለያ በማባበል የልጆቹን ፍቅር የየራሳቸውን ብቻ አድርገው ለማኖር ይታገላሉ፡፡ እናት ጋር ሲሄዱ የተለየ መስተንግዶ ይደረግላቸዋል፡፡ አባት ጋር ከሄዱም እንደዚያው የተለየ መስተንግዶ ይደረግላቸዋል፡፡ አንዴ እናት ዘንድ አንዴ አባት ዘንድ የሚዋልበት ጊዜ ይፈጠርና ልጆቹን መከታተል ያዳግታል፡፡ የሚያደርጉትንና የተሰማሩበትን ማወቅ ይቅርና የት ነበራችሁ ሲባሉ አባቴ ጋ ወይም እናቴ ጋ ምን ስታደርጉ ቆያችሁ ሲባሉ ካባቴ ጋር ስጫወት! እናቴን ስራ ሳግዝ እያሉ ምክንያት ይፈጥራሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ቁጥጥሩ

ደግሞ የህይወት ትርጉም ማጣትን የመንፈስ መረበሽን ያስከትላል፡፡

የቤተሰብ መፍረስ የሞራል ውድቀትን፣ የወመኔነትንና የወሮበላነት፣ ሲብስም የወንጀለኝነት መንስኤ ይሆናል፡፡

በዚህ አንቀፅ ውስጥ የቤተሰብ መበተን ለሚከተሉት ውጤቶች ምክንያት ሆኗል፡፡

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| -የቤተሰብ መፍረስ | -የልጆች መበተን |
| | -የወላጆቻቸውን ፍቅር ማጣት |
| | -ወመኔና ወሮበላ መሆን |
| | -በተለያዩ ሱሶች መጠመድ |

ተግባር

1.ከላይ በምሳሌ 2 የቀረበውን አንቀፅ መሰረት በማድረግ በምክንያትና ውጤት የተያያዘ ከ40 ቃላት ባልበጡ አንድ አንቀፅ ፃፉ፡፡

2.መምህራችሁ ‹‹አንድነትና ብዝሀነት››በሚል ርእስ አንድ አንቀጽ ያነቡላችኋል፡፡ ካዳመጣችሁ በኋላ ስለ አንድነት የተረዳችሁት የአንድነትን ጠቀሜታ ከ 25 እስከ 30 ባልበለጡ ቃላት አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡-ቃላት

ተግባር

በ ‹‹ሀ›› ረድፍ ለሚገኙት ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒ ፍቻቸውን በ ‹‹ለ›› ረድፍ ካሉት በመምረጥ አዛምዱ፡፡

‹‹ሀ›› ‹‹ለ››

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ማለዳ | ሀ. ተጠቃሚ |
| 2. መጥበቅ | ለ. ተከፋ |
| 3. ተጠቂ | ሐ. ወድሞ |
| 4. ፈነጠዘ | መ. ምሽት |
| 5. ለምቶ | ሠ. የጋራ |
| 6. እኩይ | ረ. መላላት |
| 7. የግል | ሰ. ሰናይ |
| 8. ጥፋት | ሸ. ልማት |
| 9. ወደቀ | ቀ. አስቀያሚ |
| 10. ማራኪ | በ. ተነሳ |

2. በ ‹‹ሀ›› ረድፍ የተዘረዘሩት ቃላት በ ‹‹ለ›› ረድፍ ከተዘረዘሩት ተመሳሳያቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1.ብልሃት | ሀ.ያልበሰለ |
| 2. ለጋ | ለ.ተጨምረው |
| 3.ገደብ | ሐ.ስልት |
| 4.ስቃይ. | መ. መፈናቀል |
| 5.ሚና | ሠ.ችግር |

6. ፍልሰት ረ. ወሰን

7. ተደምረው ሰ. ድርሻ

8. አዛውንት ሸ. ክርክር

9. ቃና ቀ. ሽማግሌ

10. ሙግት በ. ጣዕም

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

**ማስታወሻ**

**የሐረግ ዓይነቶች**

ሃረግ ማለት ትርጉም ያላቸው ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት መዋቅር ነው፡፡ በምዕራፍ ሶስት የተማራችሁት አምስቱ የቃል ክፍሎች ማለትም ስም፣ ቅፅል፣ግስ፣ተውሳከ ግስና መስተዋድድ እያንዳንዳቸው ከሌሎች ተዋቃሪዎች ጋር በመቀናጀት ሃረግ ይመሰርታሉ፡፡ የሃረጉም ዓይነት በሃረጉ ውስጥ ዋና ሆኖ በሚገባው ቃል ዓይነት ይወሰናል፡፡ ዋና ቃል ሆኖ የሚገባው ቃልም የሃረጉ መሪ ይባላል፡፡ እያንዳንዱን የሃረግ ዓይነቶች በዝርዝር ቀጥለን እንመልከት፡፡

1. ስማዊ ሃረግ፡- ስሞችን ቀኝ መሪው አድርጎ የሚመሰረት የሃረግ ዓይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- የገጠር መንገድ

የገንዘብ ፍቅር

በምሳሌዎቹ የተሰመረባቸው ቃላት የቃል ክፍላቸው ስም ሲሆን የሚገኙትም በመዋቅሩ በስተቀኝ ነው፡፡

2.ቅፅላዊ ሃረግ፡- የሚመሰረተው በቅፅል የቃል ክፍል የሚመደብ አንድ ቃል በሌላ ክፍል ከሚመደብ ቃል ወይም ቃሎች ጋር

ሲቀናጅ ነው፡፡

ምሳሌ፡- የታወቀ ውሸታም

የሽማግሌ አታላይ

በምሳሌዎቹ የተሰመረባቸው ቃላት የቃል ክፍላቸው ቅፅል ሲሆን የሚገኙትም በመዋቅሩ በስተቀኝ ነው፡፡

3.ግሳዊ ሃረግ፡- ግሶችን ቀኝ መሪው ያደረገ የሃረግ መዋቅር ነው፡፡

ምሳሌ፡- ቡና ጠጣ፡፡

ገንዘብ ቸገረው፡፡

በምሳሌዎቹ የተሰመረባቸው ቃላት የቃል ክፍላቸው ግስ ሲሆን የሚገኙትም በመዋቅሩ በስተቀኝ ነው፡፡

4.ተውሳከ ግሳዊ ሃረግ፡- ተውሳከ ግሶችን ቀኝ መሪው ያደረገ የሃረግ መዋቅር ነው፡፡

ምሳሌ፡- ፀጉሩን ዘወትር

ዐይኑን ክፉኛ

በምሳሌዎቹ የተሰመረባቸው ቃላት የቃል ክፍላቸው ተውሳከ ግስ ሲሆን የሚገኙትም በመዋቅሩ በስተቀኝ ነው፡፡

5.መስተዋድዳዊ ሃረግ፡- መስተዋድዶች በስም፣በግስ እንዲሁም በተውሳከ ግስ የቃል ክፍል ውስጥ ከሚመደቡት ቃላት ጋር በመቀናጀት የሚፈጥሩት የመዋቅር ዓይነት ነው፡፡ መስተዋድዳዊ ሃረጎች ግራ መሪ፣ ግራም ቀኝም መሪ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- እንደ ውንድሜ      መስተዋድድ ግራ መሪ ሲሆን

ከ ወንዙ ማዶ      መስተዋድድ ግራም ቀኝም መሪ ሲሆን

ተግባር

1. ቀጥሎ የቀረቡትን ሃረጎች ተውሳከ ግሳዊና ግሳዊ ሃረግ በማለት ለዩ፡፡

1. ለማለፍ ደጋግሜ

2.ቁልቁለቱን ቶሎ

3.ትናንት መጣ

4.እግሩን ድንገት

5.ተነስታ ሄደች

2. ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ሃረጎች የሃረግ ዓይነታቸውን ለዩ፡፡

1. ገንዘብ ከወንድሙ ተበደረ፡፡
2. እንደ ጦር ፈጥኖ ተወረወረ፡፡
3. ዛፉን የቆረጠው ሰው ተከሰሰ፡፡
4. ሰውዬው የአዋቂ አጥፊ ነው፡፡
5. ልጁ ስለደከመው ተኛ፡፡

## ክፍል ሰባት፡- ስነ-ፅሁፍ

ተግባር

1.ስለ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በምዕራፍ አምስት ተምራችኋል፡፡ይህን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ከቀረቡላችሁ ጽሁፎች ውስጥ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹን ነቅሳችሁ አውጡ፡፡

ሀ.ጌታቸው ከስራ የተሰናበተበትን ደብዳቤ ይዞ ለባለቤቱ ምን ብሎ

እንደሚነግራት ሲብሰለሰል ውሎ ሲመሻሽ ቤቱ ገባ፡፡ ባለቤቱ ቀኑን

ሙሉ አዲስ ዜና ልትነግረው ስትጠብቀው እንደዋለች ነገረችው፡፡ መልሱንም ሳትጠብቅ የሶስት ወር ነፍሰ ጡር መሆኗን አበሰረችው፡፡ ጌታቸው ግን ብስራቱ መርዶ ሆኖበት ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› ብሎ ለራሱ ተረተ፡፡

ለ.ማህሌት ባህር ማዶ ያለው ወንድሟን ተማምና ትምህርቷን ችላ ካለች ቆይታለች፡፡ ዘወትር ከወንድሟ ‹‹ነይ›› የሚል ቃል ለመስማት እንደ ጓጓች ነው፡፡ ይህ አጉል ተስፋዋ ያሳሰባት ጓደኛዋ ሁሌም ‹‹ላም አለኝ በሰማይ ወተቷን የማላይ›› እያለች ትተርትባታለች፡፡

2.በ‹‹ሀ›› ክፍል ለቀረቡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በትርጉም ተመሳሳይ የሚሆኑትን በ ‹‹ለ›› ክፍል ከቀረቡት በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1.ቀና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ | ሀ.የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች |
| 2.አባቷን አታውቅ አያቷን ትናፍቃለች | ለ.የወደዱትን ሲያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ |
| 3. ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ | ሐ. በሬ ባረሰው አህያ ምርቱን አፈሰው |
| 4. አተርፍ ባይ አጉዳይ | መ. የሌባን ጠበቃ አደባልቀህ ውቃ |
| 5.በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ | ሠ.ትለብሰው የላት ትከናነበው አማራት |

ማስታወሻ

ዘይቤ፡- ዘይቤ ከተራው አነጋገር በተለየ አነጋገራችንን ወይም ጽሁፋችን ስሜት እንዲሰጥ፣ ሀሳባችን ጎልቶና ደምቆ እንዲተላለፍ የምንጠቀምበት የአነጋገር ስልት ነው፡፡ በርካታ የዘይቤ አይነቶች አሉ፡፡ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. አነጻጻሪ ዘይቤ፡- ሁለት ነገሮችን በማነጻጸርና በማወዳደር የሚቀርብ የዘይቤ አይነት ሲሆን እንደ፣ ያህላል፣ይፎክራል፣ ይመስላል…የሚሉ የአማርኛ ማነጻጸሪያ ቃላት በግልጽ የሚታዩበት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ከንፈሯ እንደ ቲማቲም ቀልቷል፡፡

ጦጣ ይመስል ዛፍ ላይ መንጠልጠል ይወዳል፡፡

2. ተለዋጭ ዘይቤ፡- የአንድን ነገር ባህሪ ለሌላ ነገር በመስጠት የሚፈጠር ዘይቤ ነው፡፡ ምሳሌ፡- ምህረት ንብ ነች፡፡

ሀሴት ቆቅ ነች፡፡

3. ሰውኛ ዘይቤ፡- ሰው ላልሆኑ ነገሮች የሰውን ልዩ ልዩ ባህርያት በመስጠት የሚፈጠር ዘይቤ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ወንበሩ ተቆጣ፡፡

ጨለማው ጥርሱን አገጠጠ፡፡

4. እንቶኔ ዘይቤ፡- አጠገብ የሌለን ነገር በቅርብ እንዳለ በመቁጠር መልስ እንዲሰጥ፤ ሃሳብ እንዲሰነዝር በመጠየቅ፤ በማወያየት፣ በማጫወት የሚቀርብ የዘይቤ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ፍረደኝ ተራራው

እባክሽ አንቺ አድባር ታረቂኝ

5. ምጸት ዘይቤ፡- በቀጥታ የተናገረውን ሳይሆን ተቃራኒ ፍችውን መልእክት አድርጎ የሚቀርብ ዘይቤ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሎጋው ልጅ መጣ፡፡ (ለአጭር ሰው)

ልጁ ሲሮጥ ጆት ነው፡፡ (ለቀርፋፋ ሰው)

6. ግነት ዘይቤ፡- ነገሮችንና ሁኔታዎችን ሆን ብሎ አስቦ የማግዘፍ ወይም የማጋነን ብልሃት ነው፡፡

ምሳሌ፡- የሰማይ ስባሪ የሚያህል ዳቦ በላሁ፡፡

ልጁ የሚጠቀልለው ጉርሻ አህያ አይሸከመውም፡፡

3.የሚከተሉትን ዘይቤያዊ አነጋገሮች ከየትኛው የዘይቤ አይነት እንደሚመደቡ ለዩ፡፡

ሀ. ቁመቱ ዛፍ ያህላል፡፡

ለ. ቢፍቱ እሳት ናት፡፡

ሐ. አናግረኝ እንጂ ተራራው?

መ. ቤቱ ፈረስ ያስጋልባል፡፡

ሠ. ምድሪቱ አኮረፈች፡፡

ረ. ልጁ እንደ ኳስ ይነጥራል፡፡

የክለሳ ጥያቄዎች

1.አቶ ኩምሳ ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ሀገር ቤት ሄዱ፡፡ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ምን አይነት ሃረግ ነው?

ሀ. ስማዊ ሃረግ ለ. መስተዋድዳዊ ሃረግ

ሐ. ቅፅላዊ ሃረግ. መ. ግሳዊ ሃረግ

2 በጣም ትጉህ ሰዎች ካሰቡበት ቦታ ለመድረስ የሚከለክላቸው የለም፡፡ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ከየትኛው የሃረግ አይነት ይመደባል?

ሀ. ግሳዊ ሃረግ ለ. ቅጽላዊ ሃረግ

ሐ. ስማዊ ሃረግ. መ ተውሳከ ግሳዊ ሃረግ

3. ዳራሹን የሞላው ሕዝብ አንዱ በሌላው ላይ እየተደራረበ የሚተራመስ የንብ ሰራዊት ይመስላል፡፡ ይህ አገላለጽ የትኛውን የዘይቤ አይነት ይወክላል?

ሀ. ምጸት ለ.ግነት

ሐ.ተለዋጭ መ. ተነጻጻሪ

4. የአዋሽ ወንዝ ሞልቶ በአካባቢው የሚገኙ ቤቶችን አጥለቀለቀ፡፡ በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ በውጤትነት የሚጠቀሰው-----------ነው፡፡

ሀ. የአዋሽ ወንዝና አካባቢ፡፡

ለ. የቤቶች መጥለቅለቅ ነው፡፡

ሐ. የአዋሽ ወንዝ መሙላት ነው፡፡

መ. ወንዝና ቤቶች ናቸው፡፡

5. የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሟሉ፡፡

ሀ.ልጅ ያቦካው----------------፡፡

ለ.----------------- ሳይዘጋ ያድራል፡፡

ሐ. ላም ባልዋለበት----------------፡፡

መ. ሙት መውቀስ---------------፡፡

## ቃላት ከነፍቻቸው

| ቃላት | ፍቻቸው |
| --- | --- |
| ሀገር በቀል | የአንድ ሀገር ሀብት፣ባህል፣ልምድ |
| መነቃቃት | ዝግጁ መሆን፣መነሳሳት |
| መዋቅር | የቃላት ፣የዓረፍተ ነገሮች…አደረጃጀት |
| ምናብ | ሀሳብ |
| ምንጭ | የአንድ ነገር መገኛ መሰረት |
| ቅርስ | ጥንታዊ የሆነ ቁሳቁስ |
| ቅፅል | ተቀጥያ |
| ባዘነ | ደከመ |
| ብርቅዬ | ሁሌ የማይገኝ |
| ቦዘነ | ሥራፈታ |
| ተሞክሮ | ልምድ |
| ተሰባጠረ | አንዱ በአንዱ ውስጥ መግባት |
| ተደራሲ | አንባቢ |
| አልባሌ | የማይረባ |
| አርአያ | ጥሩ ምሳሌ |
| አቀላጥፎ ማንበብ | ያለምንም ችግር ሁሉንም ፊደሎች፣ቃላት ለይቶ ማንበብ |

| | |
|---|---|
| አንድነትና ብዙሃነት | የተለያዩ ነገሮች በአንድነት መስማማት |
| አውድ | ሁኔታ |
| አፅንኦት | ትኩረት |
| ክህሎት | ችሎታ፣ ብቃት |
| ውህደት | መጣጣም፣አንድ መሆን |
| ውስብስብ ቃላት | ብዙ ተቀጥላዎችን አብዝተው የተወሳሰቡ ቃላት |
| ውጥን | ጅምር |
| ደራሲ | ፀሃፊ |
| ገሃድ | ግልፅ |
| ጓዳ ጎድጓዳ | ሁሉም ስፍራ(ቦታ) |
| ፍንትው | ግልፅ |

## ዋቢ መጻህፍት

ሀዲስ አለማየሁ (1958) ፍቅር እስከ መቃብር:: አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

ሰይፉ መታፈሪያ (1981) ውስጠት:: አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት::

በድሉ ዋቅጅራ (1996) በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር::

አዲስ አበባ ፣ንግድ ማተሚያ ቤት::

በዕውቀቱ ስዩም (2001) ስብስብ ግጥሞች::ኗሪ አልባ ጎጆዎች፣ የሳት ዳር ሃሳቦች እና ሌሎች አዳዲስ ግጥሞች:: አዲስ አበባ፣ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር::

ባየ ይማም (2002) አጭር ቀላልና የአማርኛ ሰዋስው::አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች::

ብርሃኑ ገበየሁ (2003) የአማርኛ ስነግጥም:: አዲስ አበባ፣አልፋ አሳታሚዎች::

ከበደ ሚካኤል (1999) የቅኔ ውበት:: አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር::

ዘሪሁን አስፋው (2007) የስነ-ጽሁፍ መሰረታውያን:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::

የሻው ተሰማ (1996) ልሳነ ብዕር ከመ ልሳን ሰብዕ:: አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት::

ዳኛቸው ወርቁ (1988) የጽሁፍ ጥበብ መምሪያ::አዲስ አበባ፣ ሜጋ

ህትመት ኢንተር ፕራይዝ፡፡

ማርታ እሸቱ (2006) ኩራዝ አማርኛ ለ9ኛ እና ለ10ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ታሪኩ ፋንታዬ (2006) ምሉዕ አማርኛ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ፋርኢስት ማተሚያ ቤት፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ 2007፡፡ ባህል ቱሪዝም፡፡

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ዳግማዊ ነቃ ጥበብ፣አዲስ 1879 ያልተዘመረላቸው፣ 2007፡፡

(htt://WWW.Mor.gov.et) የገቢዎች ሚኒስቴር ድህረገፅ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓ.ም